# ተልዕኮዬ

አመሰግናለሁ፡ ወንድሜ።

2 እንዴት አመሻችሁ። (አመሰግናለሁ፡ ወንድሜ።) እንዴት አመሻችሁ ሁላችሁም። ዛሬ ማታ ጥሩ ስሜት እየተሰማኝ ነው፥ ደስ ብሎኛል። ከትናንት ማታ ከስብሰባው ጀምሮ ጥሩ ስሜት ይሰማኛል። ምስኪኗ ዓይነ ሰውር ሴት የዓይን ብርሃኗ ስትቀበል ማየቴ ለእኔ በጣም ታላቅ በረከት ነበር። እና ሌሎች ብዙ...

3 ዛሬ አንዲት ሴት፡ ምናልባትም አሁን እዚህ ትገኛለች፡ ከትናንት በስቲያ ምሽት ስብሰባ በኋላ ትናንት በሰፈሯ ስለተከሰቱት ነገሮች የነገረችኝ አበረታች ደብዳቤ ደርሶኛል፡ ጌታ ለረጅም ጊዜ ሙሉ በሙሉ የማትሰማ ለነበረች ሴት መስማትን እንዴት እንደመለሰላት የሚገልጽ ነው፡ እንዲህ—እንዲህ በማለት፡ የጌታ መልአክ እሷ ወደነበረችበት ቤት እንደገባ የመስማት ችሎታዋን እንደመለሰላት ተናግራለች። እሷም በጣም... ምስክርነቷን በስተጀርባ በኩል ብትጽፍልን፡ እንዲህ ቢሆን እንፈልጋለን። ስለዚህም፡ ይህ በጣም መልካም ነው። በዚህም ደስተኞች ነን፡ በጣም ደስ ይለናል።

4 ስለዚህም፡ የእሁድ ምሽት ስብሰባውን ልናጠናቅቅ አቅደን ነበር፡ ነገር ግን ባናደርገው እንደሚሻል ወሰንን፡ ምናልባት ለጥቂት ጊዜ ብንቀጥል ይሻላል። ልናደርግ... እንዲህ ልናደርግ ነበር... [አድማጮች አጨበጨቡ—አርታዒ።] አመሰግናለሁ። በጣም አመሰግናለሁ። በጣም አመሰግናለሁ፡ ይህ ጥሩ ስሜት እንዲሰማኝ ያደርገኛል።

5 ያንን ያደረግሁበት ምክንያት፡ እዚህ ትብብር ስለሌለ አልነበረም፡ ዳሩ ግን ለወንድም ፍሪማን ካለኝ አክብሮት የተነሳ ነው፡ እያችሁ፡ እርሱ ስብሰባ በሚያደርግበት ሰዓት ማካሄድ አልፈለግሁም። አገልግሎቱንም በምንም መንገድ እያደናቀፍኩ እንደሆነ ባስብ ኖሮ፡ አላደርገውም ነበር። ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በፊት አንዲት ትንሽ ማስታወሻ ደ—ደ—ደርሳኛለች፡ ስለዚህ አሁን የተሻለ ስሜት ይሰማኛል፡ ይሁን መ—መልካም ነገር ነው፡ ስለዚህ... አመሰግናለሁ። በጣም አመሰግናለሁ።

6 በአንዳንድ አገልጋይ ወንድሞች መካከል ትንሽ መደናገር ተፈጥሮ ነበር ስብሰባዎቻችን ተደራረቡብን፡ በአንድ ጊዜም በአንድ ከተማ ውስጥ ተገኘን። ያንን ማድረግ እንደማንፈልግ እርግጠኛ ነኝ። ሆኖም በእናንተ ላይ ለመጫን እየሞከርን እንደሆነ እንድታስቡ አንፈልግም።

7 ነገር ግን እንደሚመስለኝ፡ያዕቆብ አንድ የውሃ ጉድጓድ እንደቆፈረ አምናለሁ፡ ፍልስጤማውያንም አባረሩት፡ እርሱም ክፋት ብሎ ጠራው፥ ሌላም ቆፈረ፡ ከዚያም አባረሩት፡ እርሱም ጠብ ብሎ ጠራው፥ ሆኖም ሦስተኛውን ቆፈረና፡ "ለእኛ ለሁላችንም የሚሆን ቦታ አለ፡" አለው። ስለዚህ... አመሰግናለሁ። በጣም አመሰግናለሁ።

8 ስለዚህ፡ ከወንድም ፍሪማን ጋር በዚያች በትንሿ ከተማ፡ ቺካጎ ውስጥ በነበርን ጊዜ፡ ታዲያስ፡ ተውኩለት፡ ራቅ ብዬ ሄድኩ፡ ታውቃላችሁ፡ የነበረን

ነገር... በካሊፎርኒያ ውስጥ ግን ለሁላችንም የሚሆን ቦታ አለ፡ እዚህ ታላቅ የውሃ ጉድጓድ አግኝተናል። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። አንድ ሰው ይህች ከተማ አራት መቶ ሃምሳ ስኰዌር ማይልስ እንደምትሸፍን ነግሮኛል። ስለዚህ በቂ ቦታ አለ፡ አይደል? ብዙ፡ የታመሙ ሰዎችም፡ አሉ፡ ከእነርሱም ብዙዎቹ ለጤንነታቸው ሲሉ ወደዚህ ይመጣሉ። ስለዚህም እግዚአብሔር እዚህ ለሁለታችንም፡ ታላቅ ሰብሰባ እንደሚሰጠን አምናለሁ፡ በየቦታው ያሉትንም ሰብሰባዎች፡ እንዲሁም በየቦታው ያሉ አገልግሎቶችንና አገልጋዮችን ሁሉ እንደሚባርክ አምናለሁ።

9 ነገ፡ በሰንበት ቀን፡ እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ዘንድ፡ በየቦታው፡ ለክብሩ ብዙ ነፍሳትን እንዲሰጥ እንጸልይ። ደግሞስ፡ በቅርቡ ወደ ቤታችን እንሄዳለን፡ ታውቁታላችሁ፡ አሁን እየተዘጋጀን ነው፡ ስለዚህ ምን ሰዓት ሊሆን እንደሚችል ስለማናውቅ፡ ስለዚህ ሁልጊዜ ንጹሕ ሆነን እንጠብቅ።

10 እንወደዋለን፥ እናንተም እንደምትወዱት አንጠራጠርም ባይሆን እዚህ አትገኙም ነበር። በልባችሁ ውስጥ እግዚአብሔርን እንደምትወዱ የሚያሳይ አንዳች ነገር አለ፡ ባይኖር ኖሮ ፈጽሞ ወደዚህ አትመጡም፡ ሌላ ቦታ በተገኛችሁ ነበር። ስለዚህ፡ ይህን በማድረጋችሁ ደስተኞች ነን።

11 ስለዚህ፡ የትናንት ማታው በጣም—ታላቅ ሰብሰባ ነበር፡ ዛሬ ማ—ማታም ለጌታችን ሌላ ታላቅ ሰብሰባ እንደሚሆን እንጠብቃለን። ብቻ በረከቶቹን ይጨምርልን። እንግዲህ፡ ነገ ከሰዓት በኋላ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ነገ ከሰዓት በኋላ ልናገራችሁ እ—እፈልጋለሁ፡ እንግዲህ፡ ከፈለጋችሁ፡ መሰበክ ልትሉት ትችላላችሁ። እኔ፡ በሌላ ጊዜ እንደነገርኳችሁ፡ ስለ ሰባኪነት ከተናገርን እኔ ልክ እንደ ተጠባባቂ ጎማ ነኝ፡ ታውቃላችሁ። ይህ ማለት... ታውቃላችሁ፡ ጎማ ሲተነፍስባችሁ፡ ለመጓዝ በተጠባባቂው ጎማ ትጠቀማላችሁ። ስለዚህ እ... ዳሩ ግን የትኛውም ጎማ አልተነፈሰብንም፡ ሆኖም በማንኛውም ሁኔታ፡ ሊጠቀሙበት ነው።

12 ስለዚህ ነገ ከሰዓት በኋላ... ሁልጊዜ ከሰዓት በኋላ ለመናገር እሞክራለሁ። ሰዎቹም በባሕር ማዶ ላሉት ሚ—ሚሲዮናውያን የሚረዳ የ—የሚሲዮናውያን መባን ይሰበስቡልኛል። ራሴ ቀምሼ እስካየው ድረስ ሚሲዮናዊነት ምን እንደሆነ አላውቅም ነበር። እጅግ ድንቅ ነው፡ ግን፡ አቤት፡ እርዳታ የሚያስፈልገው አካል አለ ቢባል፡ ሁሉንም ነገር በመጋፈጥ ላይ ላለው በ-በሩቅ ግንባሮች ላይ ያለ ምስኪን ሚሲዮናዊ ነው፡ በተለይም ከተፈጥሮ በላይ ከሆነው ኃይል ጋር በመጋደል ላይ ያሉቱ።

13 ስለሆነም፡ ነገ ከሰዓት በኋላ፡ ሁለት-ተኩል ይ—ይመስለኛል፡ አይደል፡ ወንድሞች፡ የምናደርገው... ? ነገ ከሰአት በኋላ ሁለት-ተኩል ላይ። ስለ እናንተም በጣም ደስተኞች እንሆናለን፡ ቤተ ክርስቲያናችሁ አገልግሎት ከ—ከሌላት... አሁን፡ ነገ እሁድ ነው፡ የ—የራሳችሁም አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት አላቸው፡ ስለዚህ የራሳችሁ አገልግሎት ከሌላችሁ፡ ብትመጡ፡ በጣም ደስተኞች እንሆናለን። እርግጥ ነው፡ በቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ አገልግሎት ካላችሁ፡ በአገልግሎታችሁ ጊዜ በቦታችሁ መገኘት ግዴታችሁ ነው፡ እያንዳንዱ ሰው በቤተ ክርስቲያኑ። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ከሌላችሁ፡ እናንተም... ወይም ባላችሁበት ቤተ ክርስቲያን ከሌላችሁ፡ ወጥታችሁ ከእኛ

ጋር ሁኑ። በድጋሚም አስታውሱ፡ በከተማውና በየቦታው አገልግሎቶች ሁሉ በመካሄድ ላይ ናቸው። እግዚአብሔርም... እግዚአብሔር ወደ መከሩ ተጨማሪ አጫጆችን እንዲልክ ጸልዩ፡ በእርግጥም ያስፈልጉናልና።

14 ከውድ ወገኖቻችን ብዙዎቹ መጥቼ አብሬያቸው እራት እንድበላ ግብዣ እየላኩልኝ ነው፡ እ—እና፡ ኦህ፡ በእርግጥም፡ ለሁሉም ማድረግ ብችል እመኝ ነበር። ያንንም ማድረግ እፈልጋለሁ፡ ሆኖም፡ ያንን ማድረግ ለእኔ ትንሽ ይከብደኛል። ከአንዱ ጋር ሄጄ ከሌላኛው ጋር ባልሄድ፡ ከሌላኛው ይልቅ ለዚያኛው የተለየ ቦታ እንደሰጠሁ አድርገው ሊያስቡ ይችላሉ ብዬ እፈራለሁ፡ ያንንም አላደርግም። ነገር ግን ሁ—ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ፡ እንድትወዱኝም እፈልጋለሁ፡ ጌታንም የምንወድ ከሆነ፡ እርሰ በርሳችንም እንደዚያው ይሰማናል። ስለዚህ፡ ወደፊትም እነሆ... አንድ ቀን፡ ከሁላችሁም ጋር እራት ልበላ እሄዳለሁ። አሜን። ያ ድንቅ አይሆንምን? እኔ የማስበው፡ ጦርነቱ ሁሉ ካበቃና ጢሱ ከበረደ በኋላ፡ ወደ ላይ እንሄዳለን፡ ቤተሰቦቻችንን አግኝተን፡ ከዚያም እርሱን እናገኘዋለን፡ በጠረጴዛው ዙሪያ ፊት ለፊት እንቀመጣለን። ያ ድንቅ አይሆንምን? በማዕዱ ዙሪያ ክራንች ወይም ዊልቼር ፈጽሞ አይኖርም፡ ፈጽሞ አይሆንም... ኦህ፡ ታዲያ አስደናቂ አይሆንምን?

15 ከዚያም ያ ሁሉ እዚያ ተቀምጦ ሳናይ፡ ከማዕዱ ማዶ እመለከትና፡ እንዲህ እላለሁ፡ "ታዲያስ፡ እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። ማይ!" ከዚያም ደግሞ—ጥቂት እናለቅሳለን። እንደዚያ አታምኑም? ከቻልን፡ በደስታ ጥቂት እናለቅሳለን።

16 ከዚያም ከማዕዱ ራስጌ ንጉሣችን በግርማው ይመጣል፡ በእኛ በሁላችንም መካከል እያለፈ፡ እጆቹን በላያችን አድርጎ አቅፎን፡ እንዲህ ይላል፡ "ብዙ መከራ ተቀበላችሁ፡ ለእኔ ስትሉ በብዙ ነገር አልፋችኋል።" እንባን ሁሉ ከዓይን ያብሳል፡ "አሁን፡ ከእንግዲህ ወዲህ አታልቅሱ። እ—እ... ሁሉ ነገር አብቅቷል፡" ይላል። ኦህ፡ ለዚያ ታላቅ ጊዜ! ለዚህም ነው እዚህ ያለነው፡ አይደለም እንዴ? ክንዱን በዙሪያችሁ አቅፎ፡ "አሁን፡ አታልቅሱ። ወደ ጌታ ደስታ ግቡ፡ መልካሙን ገድል ተጋድላችኋል፡" ሲል መስማቱ አስደናቂ ይሆን የለ። ስለዚህ እዚህ እያለን ይህን ዕድል ሰላገኘን፡ መልካም ገድል፡ እውነተኛ ገድል እናድርገው።

17 የተወሰነ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላነብ እፈልጋለሁ፡ በቀጥታም ወደ ጸሎት መሰመር እንገባለን፡ ስለዚህ ጥሩ ጊዜ እናሳልፋለን፡ ጠዋት ለሰንበት ትምህርት እንዳታረፍዱ፡ ሰዎቹን በጊዜ እንለቃቸዋለን። ከቻልንም፡ በጣም በጊዜ የመልቀቅ፡ ልማድ ለማድረግ እየሞከርን ነው፡ ይህም ሰዎች ወደ ሥራ ሄደው፡ ለሚቀጥለው ምሽት፡ ተመልሰው መምጣት እንዲችሉ ያግዛቸዋል።

18 ለመጀመሪያ ጊዜ እዚህ የተገኛችሁ ስንቶቻችሁ ናችሁ? እጆቻችሁን አሳዩን... አቤት፡ እንዴት ድንቅ ነው! እዚህ ያላችሁ ሁላችሁም፡ አጨብጭቡላቸው... ያ ድንቅ ነው! በትክክል። አቤት፡ እናንተን እዚህ በማግኘታችን እና እናንተን በማየታችን በጣም ደስ ብሎናል። እጃችሁን በመጨበጥ እንኳን ደህና መጣችሁ ልላችሁ እመኝ ነበር። ሆኖም መንፈስ ቅዱስ በእጆቹ አቅፎ እንዲህ እንዲላችሁ፡ እጸልያለሁ፡ "እሱ ለማለት የፈለገው ይህ ነው፡ እንኳን—እንኳን ደህና መጣችሁ" ይበላችሁ።

19 አሁንም፡ በአገልግሎቶቹ ውስጥ፡ አገልግሎቶቻችን፡ በተለምዶ ከምንመጣባቸው፡ የመለኮታዊ ፈውስ አገልግሎቶች ጥቂት ይለያሉ፡ ይህም ከጥቂት ዓመታት በፊት ካገኘኹ ከተፈጥሮ በላይ ከሆነው አካል አሠራር ሥር ነው። ይህም ደግሞ በጥብቅ የባፕቲስት ትምህርት በመሆኑ፡ እ... ባፕቲስት ስለመሆኔ፡ ብዙ ጊዜ ሳነሳ ሰምታችሁኛል፡ አሁን፡ እ—እኔ—ባፕቲስት አይደለሁም፡ ክ—ክርስቲያን ነኝ፡ በቃ። አሁንም ባፕቲስት መሆን፡ ክርስቲያን መሆንም እችላለሁ፡ ተረዱት።

20 ዳሩ ግን—በቅርብ ጊዜ በሊትል ሮክ፡ እ... ክራንቾች የነበሩት አንድ ሰው ነበረ፡ ለዓመታትም... በእነርሱ ላይ ነበረ፡ ወደ ስልፉም ገባና፡ ጌታ ፈወሰው። ኦህ፡ በጣም ደስ አለው! አንዱን ክራንች በሌላኛው ላይ አንጠልጥሎ፡ በመንገድ ላይ እየጮኸ ሄደ፡ በሊትል ሮክም ሁሉ፡ ለሁሉም እየመሰከረ ወጣ።

21 እና በሚቀጥለው ምሽት፡ ወደ አገልግሎት ተመልሶ መጣና፡ ተነሰቶ፡ እንዲህ አለ፡ "ስማ፡ ወንድም ብራንሃም፡ አንተ እንዲህ ስትል ሰምቼሃለሁ... ይህን በትክክል ልረዳው አልቻልኩም" አለ። እርሱም፡ "እንግዲህ፡" እንዲህ አለ፡ "አንተ ስትሰብክ ሰሰማ፡ አንተ ናዝሪን እንደነበር እርግጠኛ ነበርኩ" አለ። እርሱም የነበረው ያንን ነው። "ናዝሪን እንደሆንክ እርግጠኛ ነበርኩ፡" አለ። እንዲህ አለ፡ "ከዚያም የጴንጤቆስጤ ሰዎችን ሁሉ አየሁ፡ እንዲሁም፡ 'አይ፡ እርሱ ጴንጤቆስጤ ነው' አልኩ። አሁን ደግሞ ባፕቲስት እንደሆንክ ትናገራለህ።" አለኝ፡ "ያ—ያንን ሊገባኝ አልቻለም።"

እኔም፡ "ኦህ፡ ይህ ቀላል ነው፡ አባቴ" አልኩት። "እኔ ጴንጤቆስጤ-ናዝሪን-ባፕቲስት ነኝ፡" አልኩት።

22 ስለዚህ፡ ያ... አዎ። እግዚአብሔር ሁላችንንም ይወዳል። በልጁ በኩል፡ በመንግሥቱ ውስጥ ዳግመኛ በመወለድ ሁላችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ነን።

23 እናም እኔ... በእውነት፡ እኔ... ያ... በሚስዮናዊ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ተሾምኩ፡ እና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሌላ ቤተክርስቲያን አልተሾምኩም። ሆኖም ወደ መለኮታዊ ፈውስ አገልግሎቶች ስመጣ፡ በወንጌላውያን መካከል፡ ለሁሉም ከየሐይማኖት ተቋም የተውጣጣ እንዲሆን አደረግኩት። ልክ... እግዚአብሔር በዚህ መስመር ውስጥ መቶዲስት፡ ወይም ባፕቲስት፡ ወይም ካቶሊክ፡ ወይም ምን እንደሆናችሁ ፈጽሞ አይጠይቅም፡ የምትፈወሱት በእምነታችሁ ነው፥ በእምነታችሁ ትፈወሳላችሁ።

24 እና፡ ዳሩ ግን ስጦታዎችና ጥሪዎች ያለ ንስሃ ናቸው አስቀድመው የተወሰኑ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆናቸውን አምናለሁ ስል፡ ይህ የባፕቲስት ትምህርት ነው ብላችሁ እንድታስቡ አሁን አልፈልግም።

25 ትንሽ ልጅ በነበርኩ ጊዜ... ዛሬ... የተወለድኩባትን ያቺን ትንሽ ጎጆ ሥዕል የሳለችው ያቺ ሴት፡ ያ በጣም ጥሩ አድርጋለች። ያኔ ስወለድ፡ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ አካል ወደ ክፍሉ መጥቶ ነበር፡ መጠኑም **እዚያ** ካሉት መብራቶች የአንዱን ያህል ነበር። እስከዚህ ጊዜ ድረስ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ተከታትሎኛል። ምን እንደነበረ አላውቅም ነበር። እ... ከእኔ በፊት የነበሩ ዘመዶቼ ካቶሊኮች ናቸው። እኔ በሁለቱም በኩል አይሪሽ ነኝ፡ በአባት እና በእናቴ፥ ለዚያም ይቅርታን አግኝቻለሁ። ስለዚህ፡ አንድ ሰው፡ እ—እ—እንዲህ

አለኝ… “አንተ አይሪሽ ነህ እንዲሁም፡ ከኬንታኪ ነህ፡ ኦህ ማይ፡ በጣም አስቃቂ ነው።” ስለዚህ… ሆኖም እግዚአብሔር ማረኝ፡ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስም በኩል ክርስቲያን አደረገኝ፡ በጣም ደስተኛ ነኝ። ከዚያም ክርስቲያን ስሆን…

26 ትንሽ ልጅ በነበርኩ ጊዜ፡ ክርስቲያን ከመሆኔ በፊት፡ ይህ ወደ እኔ ይመጣ ነበር፡ ያነጋግረኝም ነበር፡ ሊከሰቱ ያሉ ነገሮችም ያሳውቀኝ ነበር። ያም፡ እስከ ሞት ድረስ ያህል፡ ያስፈራኝ ነበር። በዚያም ምክንያት እደነግጥና እሸበር ነበር። ሆኖም ይህ… በመጀመሪያ ልክ በቁጥቋጦ ውስጥ እንደሚያሽከረክር ነፋስ፡ ቁጥቋጦ ውስጥ አነጋገረኝ፡ እናም ወደፊት እኔ የማደርገው ሥራ ስላለ፡ ፈጽሞ እንዳልጠጣ፡ ወይም እንዳልጨስ፡ ወይም ሰውነቴን እንዳላረክስ ነገረኝ። በሕይወቴም ዘመን ሁሉ፡ ጨዋ ሰው ሆኜ ለመኖር ሞክሬያለሁ፡ ዳሩ ግን በተሳሳተ መንገድ ተረድተውኝ ነበር። አባቴም ሳይቀር እንደ ሌሎቹ ብራንሃሞች ስላልጠጣሁና፡ የመሳሰሉትን ስ—ስላላደረግሁ፡ ሴታሴት ነህ ይለኝ ነበር። ሆኖም እንድጠጣ የማይፈቅድልኝ የሆነ ነገር በልቤ ውስጥ ነበረ፡ እርሱም ክርስቶስ ነበረ። እናም አንድ ሃሳብም አለኝ፡ በዚህ ላይ ትክክል ላልሆን እችላለሁ፡ እንደሚመስለኝ በእርሱ እንዲጠቀሙበት፡ እግዚአብሔር ይህን ለሕዝቡ ይጠብቀው እንደነበረ አስባለሁ። በሌላ መንገድ ልረዳው አልቻልኩም፡ ምክንያቱም በትውልዴ፡ እኔ ሌላ ነበርኩ። ማለትም፡ ዘመዶቼ ሁሉ ይጠጣሉ ወዘተ። ልክ የበቆሎ ፍሬ ብትተክሉ፡ ቢጫ የበቆሎ ፍሬ ከሆነ፡ ቢጫ በቆሎ እንደሚያፈራው ማለት ነው፡ አያችሁ፡ መለወጥ ካልተደረገ በስተቀር፡ በዚህም ጊዜ፡ እግዚአብሔር አደረገው።

27 ይህም ቆየት ብሎ፡ ይህ—ወደ እኔ ይመጣ ነበር፡ ያነጋግረኝም ነበር፡ ሊከሰቱ ያሉትንም ነገሮች ይነግረኝ ነበር። እንግዲህ፡ ከእርሱ ራቅኩ። ከተለወጥኩ በኋላ፡ በራሴው ቤተ ክርስቲያን፡ በባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ ከአንዳንድ አገልጋዮችና ከመሳሰሉት ጋር፡ ተነጋገርኩበት። እነርሱም ከእርሱ እንድርቅ መከሩኝ፡ እንዲህ በማለት፡ “ከዚህ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አይኑርህ፡ ስህተት ነው። ደግሞም፡ ማናቸውም ነገር ወደ አንተ ቢመጣ፡” አሉ፡ “እ… ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ—ነገሮች ዘመን፡ የሚፈጸሙት ከአድማስ ማዶ ናቸው።” አክለውም፡ “እኛ የምንኖረው በቃሉ ነው” አሉኝ።

28 አንድ ቀንም ፊደል እንደሚገድል፡ መንፈስ ግን ሕይወትን እንደሚሰጥ የሚያወሳውን አነበብኩ። ደግሞ፡ ላለመቀበል ሞ—ሞከርኩ። ተገንዝቤዋለሁ፡ ቁጭ አልኩና በቻልኩት መጠን በጥሩ ሁኔታ ላስብበት ሞከርኩ፡ “ጌታ ሆይ፡ ተሳስቼ እንደሆነ፡ ይቅር በለኝ፡” አልኩ። በዚያን ጊዜም፡ አንድ ሰው ወደ ክፍሉ መጣና ወደ እኔ ተራመደ፡ ቁመቱ ወደ ስድስት ጫማ የሚጠጋ ሰው፡ ዳሩ ግን በመልኩም የተዋሃደ-የቀይ ዳማ የሆነ፡ ጠቆር ያለ ጠጉሩ እስከ ትከሻው የሚደርስ፡ በሰው ክብደት ሁለት መቶ ፓውንድ ገደማ የሚመዝን ነበረ፡ እርሱም ነገረኝ ወደዚህ ዓለም የመጣሁት ለታመሙ ሰዎች እንድጸልይ እንደሆነ፡ እንዲያምኑ ካደረግኋቸውና ስጸልይ ቅን ከሆንኩ፡ ከጸሎቴ ፊት ምንም ነገር እንደማይቆም ነገረኝ።

29 ሰውነየውን ጠየቅሁት፡ እንደኛ ነገር ድሃ በመሆኔ፡ በተጨማሪም እኔ፡ ያልተማረ ሰው በመሆኔ፡ “ሰዎች አያምኑኝም፡” አልኩት። እኔም “ሰዎች እንዲያምኑኝ ማድረግ አልችልም፡” አልኩት።

30 እርሱም ለነገሥታትና ለገዢዎች፡ እንዲሁም ለመሳሰሉት እንደምጸልይ ነገረኝ፥ ያንን ማመን ከበደኝ። የመሰረተ ትምህርት ትምህርት ያለው ልጅ፡ ለነገሥታትና—ለገዢዎችም መጸለይ የሚለው ነገር፡ ማመኑ እጅግ ከበደኝ። ሆኖም፡ እርሱ ፈጽሞ ስህተት የሆነ ነገር ነግሮኝ እንደማያውቅ አውቅ ነበር፡ ደግሞ አጠገቤ ቆሞ ነበር። ድምፁን ሰምቻለሁ፡ ምልክቶችንም አይቻለሁ።

31 ከዛሬ አሥራ ሁለት ዓመት በፊት ገደማ፡ ጄፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና ውስጥ ካካሄድኩት አንዱ ሪቫይቫል በኋላ በአሁኑ ጊዜ መኖሪያዬ በሆነው፡ ማለቴ፡ ቤቴ ባለበት፡ በኦሃዮ ወንዝ ዳርቻ ቆሜ፡ የመጀመሪያውን ቡድኔን እያጠመቅሁ ነበር በዚያም… [በቅጂው ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]… ብዙዎች ተሰብስበው ነበር። እያጠመቅሁም ሳለ፡ በሰኔ ወር፡ ከሰዓት በኋላ ሁለት ሰዓት ላይ ነበር፡ አሥራ ሰባተኛውንም ተረኛ በስፕሪንግ ስትሪት ግርጌ በሚገኘው በኦሃዮ ወንዝ ውስጥ በውሃ እያጠመቅሁ ሳለሁ፡ የሆነ ነገር ሲናገር ሰማሁ፡ የሆነ ነገርም ሲይዘኝ ተሰማኝ። ቀና ብዬም ተመለከትኩ፡ ቀና ብዬም ሳየው፡ ከላይ ከክብር ወደታች እየተሽከረከረ የሚወርድ ነገር እኔ ወዳለሁበት መጣ።

32 **የኩሪየር ጆርናል** ጋዜጣ ስለዚህ ነገር አንድ ጽሑፍ ጽፏል፡ እንዲህ በማለት፡ "አንድ የአጥቢያ ባፕቲስት ፓስተር በወንዙ ውስጥ ሲያጠምቅ አንድ ምሥጢራዊ ኮከብ በላዩ ላይ ታየ።" ሊረዱት አልቻሉም። ኦህ፡ ምናልባትም እስከ አሥር ሺህ የሚደርሱ ሰዎች እኔ ወዳለሁበት ሲወርድ፡ ተመልሶም ወደ ሰማያት ሲወጣ አይተዋል፡ ልክ እኔ ወዳለሁበት መጣና ተመልሶ ወደ ሰማይ ወጣ። እንግዲህ፡ እ… ብዙዎች ምን ማለት እንደሆነ ጠየቁኝ፡ እኔም "አላውቅም፡" አልኩ።

33 ሆኖም ይህ ሲመጣ፡ ሲነግረኝም… በዚህ ጊዜ በመልኩ፡ እርሱ ሰው ነበረ። ሰዎች አያምኑኝም ብዬ እንደምፈራ በነገርኩት ጊዜ፡ እውነት እየተናገርኩ እንደሆነ ለእናንተ ሰዎች ወይም ለማንኛውም ሰው ለማጽናት፡ ወይም፡ በሌላ አነጋገር፡ ለሰዎች ግልጽ ለማድረግ፡ ለነቢዩ ሙሴ እንደተሰጡ ሁለት ምልክቶች እንደሚሰጡኝ ነገረኝ። አያችሁ? ያ ነው።

34 አሁን፡ ሰው ማንኛውንም ነገር ሊናገር ይችላል፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ያ እውነት እንደሆነ መልሶ ካልተናገረ፡ ያ እውነት አይደለም፥ እግዚአብሔር እውነት ነው ብሎ ከመሰከረ ግን፡ እኔ አምናለሁ፥ እግዚአብሔር ከተናገረ፡ አምነዋለሁ። አሁን፡ ያ እውነት እንደሆነ እንድታምኑ እፈልጋለሁ።

35 አንደኛው፡ የሰዎችን እጅ በመያዝ በሽታዎችን እንደማውቅ ነገረኝ። ትህትና ካለኝ፡ እና—እና ከቀጠልኩ፡ በተወሰነ ጊዜ ሰዎች ባለፈው ሕይወታቸው ያደረጉትን ነገሮች ለማወቅ ወደምችልበት ደረጃ እንደሚደርስ፡ እና—እና በፊታቸው የሚሆነውን ልነግራቸው እንደምችል ነገረኝ።

36 ከዚያም ለጥቂት ጊዜ ሳሰብ፡ እኔም ብዙ ጊዜ ወደምጠቅሰው ስለ የናዝሬቱ ኢየሱስ ወደሚያወራው መጽሐፍ ቅዱስ ጠቀስ፡ እርሱን በተሳሳተ መንገድ እንደተረዱት አውቃለሁና፡ እኔንም በተሳሳተ መንገድ እንደሚረዱኝ አሳወቀኝ፥ እነሆም ብዙዎች በተሳሳተ መንገድ ተረድተውኛል። ነገር ግን ብዙዎች መልእክቱን ስላመኑ ምስጋናየ ብዙ ነው። ኢየሱስንም በተሳሳተ መንገድ ተረድተውት ነበር።

37 አንድ ጊዜ አንድ ሰው ወደ እርሱ መጣ፡ ናትናኤል ወንድሙን ይዞ መጣለት፡ ይህ መልአክ የጠቀሰው ልክ እዚያ ላይ ነው፡ ማ—ማለቴ፡ ፊልጶስ ሄዶ ናትናኤልን አመጣ፡ እርሱም በመጣ ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ "ተንኮል የሌለበት፡ እውነተኛ እስራኤላዊ እነሆ" አለ!

እርሱም አለው፡ "መምህር ሆይ፡ ከወዴት ታውቀኛለህ? "

እርሱም፡ "ፊልጶስ ሳይጠራህ፡ ከበለስ በታች ሳለህ" አለው።

38 ልቡንም መረመረ። አሁን፡ ወደ ኋላ አፈግፍጎ፡ "በዚህ ውስጥ የሆነ ዓይነት ምትሃት አለ፡" ሊል ይችል ነበር። ያገኘውን በረከት ፈጽሞ ላያገኝ ይችል ነበር። እርሱ ግን፡ "አንተ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ የእስራኤል ንጉሥ ነህ" አለው። ወድቆም ሰገደለት፡ ለእግዚአብሔርም ምስጋናን አቀረበ። ኢየሱስ እኔ እንዲህ ነኝ ብሎ ያለውን ሆኖ ለእርሱ ካጸናለት በኋላ ልቡ ለመቀበል ዝግጁ ነበረ።

39 ከዚያም አንዲት ሴት፡ አንድ ጊዜ በውሃ ጉድጓድ አጠገብ ወደ እርሱ መጣች፡ ከመንፈሷ ጋር ለመገናኘት ለጥቂት ጊዜ አነጋገራት፡ እርሱም፡ "ሂጂ ባልሽን ጠርተሽ ነይ፡" ብሎ ተናገራት።

እሷም፡ "ምንም ባል የለኝም" አለች።

እርሱም፡ "መልካም ተናገርሽ፡ አምስት ነበሩሽ፡ አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም" አላት።

40 እሷም፡ "አንተ ነቢይ እንደሆንክ አያለሁ" አለች፡ ወዘተ። ሄዳም ለወገኖቿ፡ "ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው፡ ኑና እዩ" ብላ ነገረቻቸው። ትንሽ ተደንቃ ነበር፡ ገና ሁሉንም ነገሮች አልነገራትም፡ ሆኖም ግን ምንም ቢሆን ያውቀዋል... አሁን ይህንን ተመልከቱ፥ ኢየሱስ ያንን እንደሚያውቅ አውቃለች፡ እሱ ሁሉንም ነገሮች ያውቃል። አያችሁ? በትክክል። እግዚአብሔር እንደሚገልጥላት ያህል እንደሚያውቅ፡ ሁሉንም ነገር ያውቃል።

41 አሁን ካስተዋላችሁ፡ ውድ ክርስቲያን ወዳጄ፡ አብረኸኝ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ሆይ፡ ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ ከራሱ አንዳች እንዳላደረገ፡ ዳሩ ግን አብ በራእይ ያሳየውን ብቻ እንዳደረገ መሰክሯል። ልክ ነው? በትክክል። አያችሁ? አብ ባሳየው ብቻ ነው። አያችሁ? እንዲህ ብሏል፡ "እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ልጅ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፡ አብ የሚያሳየው ግን፡ ልጅ ደግሞ ያደርጋል።"

42 አልዓዛር በሞተ ጊዜ አስተውላችኋል? ኢየሱስ፡ መጥቶ አልዓዛርን እንዲጸልይለት መልዕክት ላኩበት፡ እርሱ አልመጣም፡ ዝም ብሎ መንገዱን ቀጠለ። ለምን ይሆን። አልዓዛር መሞት እንዳለበት ራእይ አይቶ ነበር። ስለዚህ መንገዱን በቀጠለ ጊዜ፡ መጽሐፍ ቅዱስን በደንብ ካስተዋላችሁ፡ መንገዱን ቀጠለ፡ ደግመው ላኩ፡ ፈጽሞ አልመጣም፡ ቀጠለ። ከዚያም እርሱ... ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ "ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቷል" አላቸው። ወይም፡ "ሞቷል፡" በግልጽ ቃላት ነገራቸው። ስለዚህም፡ "ነገር ግን ስለ እናንተ፡ እዚያ ባለመኖሬ ደስ ይለኛል፡ ዳሩ ግን ሄጄ አነቃዋለሁ" አላቸው።

43 አሁን፡ በዮሐንስ ወንጌል 5፥19 ቃሉ መሰረት፡ ምን ሊከሰት እንዳለ አብ አስቀድሞ አሳይቶት ነበር፡ ምክንያቱም፡ "አባት ካላሳየው በቀር ልጅ ከራሱ

ምንም ሊያደርግ አይችልም" ብሏል። ልክ ነው? በመቃብሩም ዘንድ፡ ጸሎቱን ተመልከቱ። እርሱም፡ "ድንጋዩን አንሡት" አላቸው። ሆኖም የሚያስነሳው ከሆነ፡ ድንጋዩን ለምን ያነሱታል? ሴቶቹ የሚያደርጉት ነገር ነበራቸው፡ አያችሁ። እርሱም፡ "ድንጋዩን አንሡት" አለ።

44 እርሱም፡ "አባት ሆይ፡ አስቀድመህ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ። ዳሩ ግን በዙሪያዬ ስለቆሙት ይህን አልኩ" አለ። ዝም ብሎ የተለመደ ጸሎት አደረገ፡ እንደወትሮው... እነርሱን ለማሳወቅ ያህል፡ ከዚያም አልዓዛርን ከ—ከሙታን አስነሳው።

45 አሁን፡ ያው... ጌታችንም እነዚያን ነገሮች ሲያደርግ፡ እነዚያንም ትንቢቶች ሲናገር፡ አብ ያሳየውን ብቻ ተናገረ፡ ብቻ... በአንድ ወቅት ሁለቱ አህዮች የት እንደታሰሩ አውቆ ነበር፥ በአንዲት ደርብ ቤት የት መዘጋጀት እንዳለበትና አንድ ሰው ማሰሮ እንደሚሸከም አውቆ ነበር።

46 እንግዲህ፡ እኔ መናፍስት ጠሪ ነህ ተብዬ ተከሰሼያለሁ፡ መናፍስት አነጋጋሪ ተብዬ ተከሰሼያለሁ። እናም በቀደም አንድ ሰው ሲያናግረኝ... እንዲህ አለኝ፡ "የየትኛው አባል ነህ... "

47 "**እኔ ነኝ፡**" ወይንም እንደዚያ የሚባል ቤተ ክርስቲያን ባለቤት የሆኑ የሰዎች ቡድን ኖሮ ያውቃል?

አንድ ሰው **እኔ ነኝ**" ከሆንኩ ጠየቀኝ።

እኔም፡ "አይ፡ **እርሱ ነው**፡ እና እኔ የእርሱ አገልጋይ ነኝ" አልኩት።

እርሱም፡ "እዚያ **እኔ ነኝዎች** በነበሩበት ቦታ ሰብሰባ እያካሄድክ አይደለም እንዴ? "

እኔም፡ "**እኔ ነኝ** አሁንም እዚያ አለ።" **እኔ ነኝ**፡ ያ ጌታችን ኢየሱስ ነው፡ የእኛ—አምላካችን፡ አባቱ ነው፡ "**እኔ እኔ ነኝ**።"

48 አሁን፡ ይህ በተሳሳተ መንገድ ለተረዳችሁት፡ ውድ ክርስቲያን ወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ጸጋ፡ እ—እ—እኔ ከእነዚህ ውስጥ አንዳቸው አይደለሁም፡ ወንድማችሁ ነኝ፡ እ—እኔ ወንድማችሁ ነኝ። እንደ አንዳንድ ታላላቅ ኃያል ሰባኪዎች፡ ጩኸታም አልሆንም፡ አፍርሼም መገንባት፡ መንቀጥቀጥም አልችል ይሆናል፡ ነኝ ብዬም አልሞግትም። ዓይናፋርነቴን ደግሞ፡ ምንም ላደርገው አልችልም፡ እግዚአብሔር የፈጠረኝ እንደዚያ ነው፡ መሆን ያለብኝ—የሆንኩትን ብቻ ነው። በቃ። እርሱ እንድሆን የሚፈልገው እንደዚያ ነው፡ መሆን ያለብኝ እንደዚያ ነው። እርሱ አድርግ ያለኝን ብቻ አደርጋለሁ። እናም፡ መጀመሪያ፡ ያ ይጎዳኝ ነበር...

49 አንድ ጊዜ ክሊቭላንድ ውስጥ በቅርብ ጊዜ በነበረ ሰብሰባ፡ አንድ ጥቁር ሰው ወደ ላይ ወጣና፡ እንዲህ አለ፡ "ዕድሌን ለማስተንበይ የጸሎት ካርድ ላገኝ እችላለሁን? "

50 ኦህ፡ ማይ! ለእኔ፡ ያ... እግዚአብሔር በዚያ ምስኪን ወንድም ላይ ያንን እንዳይቆጥርበት እጸልያለሁ፡ ጠጥቶ ነበር፡ ሆኖም እርሱ—እርሱ... እግዚአብሔር እንደማያደርገው አምናለሁ። አስታውሱ፡ እዚያ መንፈስ ቅዱስን ልትሳደቡ ትችላላችሁ፡ ተመልከቱ። አያችሁ?

51 ምንም እንኳን፡ ወዳጆች ሆይ፡ ሰይጣን ከዚህ ንድፍ ጋር የተያያዘ፡ ወይም የእግዚአብሔርን ነገር የሚያስመስል ነገር ቢኖረውም፡ ያሉት ነገሮች ሁሉ፡ እግዚአብሔርን ለማስመሰል ማድረግ ነበረበት። ሆኖም የ—የሐሰት ነገር ባለበት፡ ከእውነተኛ ነገር የተሰራ የሆነ ቦታ ላይ መኖሩ ግድ ነው፡ አለበለዚያ ሐሰተኛ አይሆንም ነበር። ልክ ነው? ሐሰትኛ ዶላር ሲኖራችሁ፡ እንግዲህ፡ የሆነ ቦታ ላይ—እውነተኛ ዶላር መኖር አለበት፡ ወይም ካልሆነ፡ ያ ኦሪጂናል ነው፡ አያችሁ፡ ሐሰተኛ አይሆንም።

52 ዳሩ ግን፡ ኢየሱስንም በተሳሳተ መንገድ ተረድተውት ነበር። እርሱ ተሰቀለ። ብዔልዜቡል፥ እና ብዔልዜቡል፥ ሟርተኛ ነው፡ ወይም ጋኔን ብለው ጠሩት። ብዔልዜቡል ማለት ዲያብሎስ መሆኑን ታውቃላችሁ? የአጋንንት አለቃ ነው። እነርሱም የእርሱን ሥራ፡ ነገሮችን አስቀድሞ ሊናገር ሊከሰቱም ያሉትን ነገሮች ሊያይ የቻለበትን የ—የእርሱን ተግባራት መቻሉ፡ አጋንንትን ማውጣጡ፡ በአጋንንት አለቃ፡ በብዔልዜቡል ኃይል ነው አሉ። ኃይሉ ከነቢያት ሁሉ እጅግ የላቀ እንደነበረ ያውቁ ነበር። ማናቸውም ነቢያት ከነበሩበት ደረጃ በላይ እንደነበረ ያውቁ ነበር፡ ያውቅና ይረዳ ነበርና፡ እርሱ እንዳለውም፡ አብ ከእርሱ ጋር እንደነበረ፡ እግዚአብሔርም ኢየሱስ ይናገር የነበረውን እውነት መሆኑን ያጸና ነበር። የሐይማኖቱ ዓለም፡ የውጪው የቤተ ክርስቲያን ዓለም ግን እንዲህ ያሉት እነርሱ ነበሩ፡ "እርሱ ብኤልዜቡል ነው፡ በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል።"

53 አስተውላችኋል? ዲያብሎሶች ሲገናኙት ግን፡ እንዲህ አሉ፡ "ማን እንደሆንክ እናውቃለን፡ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ።" በትክክል። እነርሱም ሥልጣኑን አወቁ።

54 እንግዲህ፡ "ባለቤቱን ብዔልዜቡል ቢሉትስ፡ ደቀ መዛሙርቱን እንዴት አብልጠው አይሏቸውም? " ምን ለማለት እንደፈለግኩ ገባችሁን?

55 እዚህ የተገኘሁት ስህተት ለመሥራት ልሞክር እንደሆነ አድርጌ ለማንም እንዳላስመስልኩ ተስፋ አ—አደርጋለሁ። አ—አታላይ ለመሆን ከምሞክር ባልሞክርና ወደ ቤቴ ብሄድ እመርጣለሁ።

56 ባለፈው ሌሊት በሕንፃው ውስጥ አንድ ሰው ነበር፡ እኔ አታላይ እንደሆንኩ፡ በጣም ጠንካራ የሆነ፡ ስሜት ነበረው። ስለዚህም አወቅሁት፡ ለልጄም ስለዚህ ነገር ነገርኩት። ዛሬ ደግሞ ከነበረች አንዲት ሴት ደብዳቤ መጣ፡ ልጄም ዝቅ ብሎ ተመለከተና፡ እንዲህ አለ፡ "ተመልከት፡ አባዬ። ልክ አንተ እንዳ... "

እኔም አልኩት፡ "አዎን። እንደሚመጣ አውቄ ነበር፡ አየህ፡ ምክንያቱም እርሱ መምጣቱን አሳይቶኛልና።" "በቀደም ሌሊት እዚያ ነበር፡" አልኩት።

57 እዚያ ኋላ ተቀምጦ ለነበረው ሰው፡ "እኔ አታላይ አይደለሁም፡" ብዬ ስናገር ሰማችሁኝ? እኔ አስመሳይ እንደሆንኩ እንደተናገረ፡ ያንን እንዳሰበ አውቄ ነበር። እንግዲህ፡ እኔ አስመሳይ ከሆንኩ፡ ተሳስቼ እንደሆነ መጥታችሁ አረጋግጡ፡ በ—በትክክል። አያችሁ?

58 ልክ እናንተ ክርስቲያን እንደሆናችሁ ሁሉ፡ እ—እ—እኔ ከጌታ ባርያ በ—በቀር ሌላ አይደለሁም። አያችሁ? በራሴም ምንም ማድረግ አልችልም፡ ጌታ የሚያሳየኝን ብቻ፡ ያንን ማድረግ እችላለሁ፡ እርሱ እንዳደርግ ከሚያሳየኝ በላይ ምንም ማድረግ አልችልም። በእነዚህም ራእዮች ውስጥ፡ ሊከሰቱ ያሉትን ነገሮች ያሳየኛል፡ ሰዎች ያደረጓቸውን ነገሮች ያሳየኛል።

59 ለመጀመሪያው፡ ለሁለት ዓመታት ያህል፡ ወይም፡ ከሁለት ዓመት ትንሽ በላይ፡ ለሦስት ዓመታት ያህል፡ የማውቀው ብቸኛው መንገድ የአንድን ሰው እጅ እጄን ሲይዝ እና በእጁ—ላይ እንግዳ የሆነ መልክ ሲኖረው ነበር። ምናልባትም እግዚአብሔር ያ ትንሽ መደናገር እንደሚፈጥር አውቆ ይሆናል። ፍቃዳችሁ ከሆነ ከልቤ የሆነ አንድ ነገር ልናገር? አያችሁ? ብዙ ሰዎች ወጥተው ከዚያ በኋላ በእጃቸው እንግዳ ስሜቶች ነበሯቸው፡ ታውቃላችሁ፡ በእጄ ባለው በሆነ ስሜት ሰዎችን እንደምፈውስ በማሰብ የተሳሳተ ግንዛቤ ይዘው ነበር። ብዙዎች ወደ እኔ ይመጡና፡ "ወንድም ብራንሃም፡ የመፈወስ ኃይል እንዳለኝ ዳሰስህ እይ፡" ይሉኝ ነበር።

60 በጭራሽ፡ አሁን ልንገራችሁ፡ የላችሁም። ያለው ብቸኛ የመፈወስ ኃይል በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ነው። በትክክል። በቃ። ይኸው ነው! ማድረግ የምትችሉት ብቸኛው ነገር ሰዎችን ወደዚያ ማመላከት ነው። ላደርገው የምችለው ያ ብቻ ነው፡ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ሊያደርገው የሚችለው አስቀድሞ ወደ ፈወሳቸው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ማመልከት ነው። በቀራንዮ በሞተ ጊዜ፡ ታላቁን ዋጋ ከፈለ። ከፈለ... በቀራንዮ የሞተላቸው የቤዛነት በረከቶች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ቀድሞውኑ ተከፍሎላቸዋል፡ ዕዳው ሙሉ በሙሉ ተከፍሏል፡ በእግዚአብሔርም ፊት ነፃ ወጥታችኋል፡ ከጭማድ ቤት ውስጥ ወጥታችኋል። በትክክል። ማድረግ ያለባችሁ ብቸኛው ነገር፡ በክርስቶስ ያለውን እምነት መቀበልና፡ ከጭማድ ቤት ወጥቶ መሄድ ነው፡ አለቀ።

61 እርሱ ዋርሳችን ነው። ልክ አይደለምን? እግዚአብሔር ሥፍራችንን ሊወስድ፡ ለእኛ የሥጋ ዘመድ ሊሆን በሥጋ ተገለጠ። በሩት መጽሐፍ፡ በዘጸአት፡ በመሳሰሉትም ውስጥ፡ በደንብ ይሰብካል፡ ለእግዚአብሔር ዘመዶች እንዴት እንደምንሆን እዚያ ያስተምራል፡ እግዚአብሔርም ወርዶ በልጁ፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ አደረ፡ ለእኛም የሥጋ ዘመድ ሆነን። እርሱም ዋርሳችን ነበረ። ቦዔዝ ኑኃሚንን በእርግጥ እንደተቤዣት ለማሳየት ጫማውን እንዳወለቀ፡ ኑኃሚንንም በመዋጀት፡ ሙሽራይቱን ሩትን እንዳገኘ፡ በእስራኤል በሮች አጠገብ የአደባባይ ምስክርነት ይደረግ ነበረ።

62 ኢየሱስም፡ እስራኤልን በዋጀ ጊዜ፡ የአሕዛብን ሙሽራ አገኘ። የአደባባይ ምስክርነትም ሰጠ፥ ከኢየሩሳሌም በሮች ውጭ፡ በሰማይና በምድር መካከል እንደ እርማ ከፍ አለ። ከፍተኛ ዋጋ የተከፈለው እዚያ ላይ ነው፡ የተቤዠን ቦታ ያ ነበር። ጠፍቶ የተነረው ርስታችን በሙሉ፡ ጤንነታችን፡ ጥንካሬያችን፡ መዳናችን፡ በዚያ በውድቀቱ ውስጥ የጠፋው ሁሉ በቀራንዮ ተዋጀ። ይኸው ነው።

63 ወንድሜ፡ እህቴ፡ ምን ያህል አሳምራችሁ መጸለይ እንደምትችሉ፡ ወይም ምን ያህል ንስሐ ማድረግ እንደምትችሉ አይደለም፡ እርሱ እንዳደረገላችሁ ለማመን እምነታችሁ ነው ወደ ፊት የሚያመጣችሁ ያ ነው። በትክክል። ዛሬ ማታ እያንዳንዱ ኃጢአተኛ በጆሆቫ በእግዚአብሔር ፊት ድኗል፡ ዳሩ ግን እስክትቀበሉት፡ እስክታምኑበት፡ እስክትናዘዙትም ድረስ ምንም አይጠቅማችሁም፡ ከዚያም በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለው እንዲያደርገው እርሱ የኑዛዜያችሁ ሊቀ ካህናት ነው።

64 ማናቸውም የቤዛነት በረከቶች፡ ከደከማችሁ፥ "እርሱ ስለ መተላለፋችን

ቆስሏ፡ ስለ በደላችንም ደቀቀ፥ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።" አስቀድሞ ተፈጽሟልና፡ እናንተ ብቻ ተቀበሉት።

65 አሁን፡ አገልጋይ ቃሉን ወስዶ ሊያብራራው ይችላል። እኔ ያልተማርኩ ነኝ፡ ስለ ቃሉ ብዙ አላውቅም፡ እግዚአብሔር ለእኔ የገለጠልኝ የድነት እቅድ እና ነገሮች ብቻ ነው። በሴሚናሪ ወይም በትምህርቶች ፈጽሞ አልመጣም፡ የመጣው በመንፈስ መገለጥ ብቻ ነው። የማውቀውንም፡ እግዚአብሔር እንደሰጠኝ አውቃለሁ። ከዚያም፡ ስለ ቃሉ ብዙ ሳላውቅ፡ እውነትን እየነገርኳችሁ እንደሆነ ለእናንተ ሰዎች ማጽናት ሊሆኑ የሚችሉትን እነዚህን ሌሎች ነገሮች ሰጠኝ።

66 እግዚአብሔርም ሁሉንም ያውቃል... በሚሊዮኖች ፊት ሰብኬያለሁ፡ ሆኖም በዚህ ውስጥ ምንም ድርሻ እንዳለኝ የተናገርኩበት ጊዜ ፈጽሞ አልነበረም። ክብር ሁሉ እዚያ ለዋጃችሁ፡ ለእግዚአብሔር ልጅ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ይሁን። እኔ መናገር የምችለው እሱ ሲናገርና ሲናገር ብቻ ነው። ዛሬ ማታም አምናለሁ፡ ዛሬ ማታ ከዚህ ሕንፃ ወጥቼ ዳግመኛ ፈጽሞ ባልመለስ፡ እናንተ ሰዎች በሰብሰባዎቼ ውስጥ የነበራችሁ ሰዎች፡ በአገሪቱ ውስጥም ሆነ ከአገሪቱ ውጭ ባለ በማንኛውም ቦታ ህመምተኛው ማንም ቢሆን ምን፡ መቼም ሆነ የትም ቢሆኑ፡ ምስክርነት መስጠት እንደሚኖርባችሁ፡ አምናለሁ...

67 ባለፈው ቀን እዚህ ታች መናፈሻው ውስጥ እንዳገኘኋት ሴት፡ መናፈሻውን አቋርጣ እየመጣች ነበር፡ ከኢሊኖይ መጥታ ነበር፡ በጣምም ታማ ነበር፡ መናፈሻውንም አቋርጣ መጣችና፡ "ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም፡" አለች፡ እዚያው ጀመረች፡ እኔም በአጠገቧ ተቀመጥኩ። በዚያም መንፈስ ቅዱስ ወደ ኋላ አስታወሳት (አሁንም እዚህ ትገኝ ይሆናል፡ እንዳለች አገምታለሁ።)፡ እርሱም ወደ ኋላ ተመልሶ በሕይወቷ ውስጥ ያለፈችበትን ሁሉ ነገራት፡ እዚያ መናፈሻው ውስጥ ተቀምጠን፡ አያችሁ፡ ስለ...

68 ከእናንተ መካከል ማንም ቢሆን፡ በበሽተኛው ላይ ያለውን ችግር፡ ባለፈው ሕይወታቸው ውስጥ የነበሩትንም ነገሮች፡ ምን እንደነበረ፡ ሲናገር እንጂ ሌላ ያያችሁት ጊዜ የለም። ልክ ነው? ያም... ያ እውነት መሆኑን ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? አሁን፡ ያንን ለ—ለማጽናት ያክል እጆቻችሁን አንሱ። አያችሁ? አሁን፡ ያ አይፈውሰም፡ ያ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እዚህ ስለመገኘቱ ማረጋገጫ ብቻ ነው።

69 ባለፉት ሁለት ምሽቶች፡ ወዳጆች ሆይ፡ ሰዎቹን በራሳቸው እምነት ላይ ብቻ ለቀናቸው፡ እዚህ አሳልፈናቸዋል፡ እዚህ ቆሜ የጀማሪነት ሚና ለመውሰድ ብቻ ሞክሬያለሁ፡ ብቻም፡ ሰዎቹ ሲመጡ፡ እነርሱን ከማነጋገር በመቆጠብ፡ ለእነርሱ በመጸለይ ብቻ እዚህ እንዲያልፉ አደረግኩ፡ እግዚአብሔርም ለእኛ ድንቅ ነገሮችን ሠርቷል። በዚህም ደስተኛ ሆኜ ተደንቄያለሁ፡ ምክንያቱም ብዙ ሰዎችን ማስተናገድ ስለቻልኩ። ብዙውን ጊዜ አንድ-በ-አንድ፡ አንድ-በ-አንድ እስተናግዳቸዋለሁና፡ ተገቢውን የሰዎች ቁጥር ለማዳረስ... በጣም ረጅም ጊዜ ይወስዳል። አሁን ግን በየምሽቱ አምሳ ሰዎችን ማስተናገድ ወደምችልበት ደረጃ እየደረስኩ ነው። ከሳምንቱም በፊት፡ በሚቀጥለው ሳምንት፡ በየምሽቱ

መቶ ወይም ከዚያ በላይ እንደማደርግ አምናለሁ። እግዚአብሔር እንደሚችል አምናለሁ...

70 እያንዳንዳችሁም፡ እዚህ ስታልፉ፡ ሁኔታችሁ ምንም ይሁን ምን፡ ኢየሱስን እንደ ግል ፈዋሻችሁ አድርጋችሁ እንድትቀበሉት፡ ሳይሰማችሁም ሆነ ከሌላ ከማንኛውም ነገር በፊት አምናችሁ፡ መስክራችሁ፡ መፈወሳችሁን አውጃችሁ ከዚህ እንድትወጡ እፈልጋለሁ።

71 አሁን፡ ትናንት ማታ የነበረችው አሮጊቷ ዕውር እመቤት፡ ያችን ምስኪን አሮጊት ወደ መድረኩ አመጧት፡ ልክ... እርግጥ ነው፡ ቅባቱ በጣም ጠንካራ ከመሆኑ የተነሣ፡ በመስመሩ ውስጥ ልክ የመጀመሪያዋ ነበረች። “ቁጭ አርጓት፡” አልኩ፡ ከአፍታ በኋላ ወደ እሷ መድረስ እንደምችል አሰቤ ነበር። ዕውር በመሆኗ፡ ከነገሮች ጋር ስትጋጭ አየሁ፡ ሊያስቀምጧትም––ሞከሩ። አቋርጣ መጣች፡ እጆቼንም በላዩዋ ላይ ጭኜ ባረክኋት። አልፋ መሄድ ስትጀምርም፡ መንፈስ ልክ እንዳዞራት፡ ወደዚያው ጎተተኝ፡ ያኔ እንዳበቃ አወቅሁ፡ ከዚያም ወዲያውኑ፡ እይታዋን ተቀበለች። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እዚያ ኋላ ተቀምጣ እያነበበች እንደሆነ አንድ ሰው ነግሮኛል። እግዚአብሔር እንዴት እንደባረካት! ምስጋናችን ምንኛ ብዙ ነው!

72 መስማት የተሳናቸው የነበሩ ሌሎችም፡ ዲዳ የነበሩ አንዳንዶችም፡ ከተለያዩ ዓይነት በሽታዎች ሁሉ ጋር በሰብሰባው ውስጥ ተፈውሰዋል። አሁን፡ ታላላቅ ነገሮችን እንጠብቃለን። እዚህ ወንበር ላይ ተቀምጣ ታማ የነበረችን አንዲት ትንሽ ሴት በአጋጣሚ ተመለከትኩ። አሁን፡ እግዚአብሔር ለሁሉም መሐሪ ይሁን።

73 አሁን፡ የጸሎት መስመራችንን ማስጀመር እንድንችል፡ ፈጠን ብዬ የተወሰነ መጽሐፍ ቅዱስ ላነብ እፈልጋለሁ። እንዲጸለይላችሁ ዝግጁ ናችሁ? በሙሉ ልባችሁ አምናችኋል? ኦህ፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

74 በደጃፋችን ውስጥ ያላችሁ እንግዶች፡ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ በሽታዎችን መለየት––እይታችሁ ላታውቁ ትችላላችሁ። መንፈስ ቅዱስ ምን እንደሚያደርግ አላውቅም። ምናልባት በሰልፉ ውስጥ ያለውን ሰው ይይዝ ይሆናል፡ ወይም አንድ ሰው ምን ችግር እንዳለበት፡ ወይም በሕይወታቸው ውስጥ ያለ ነገር ይጠይቀኝ ይሆናል፥ በመድረኩ ላይ የሚያልፍ ኃጢአተኛ ሰው ሊኖር ይችላል፡ ልክ እዚያው ላይ ጠርቶኝ ሊያቆመው ይችላል። ብዙውን ጊዜ፡ በሰብሰባው ውስጥ ከቆዩና በጣም ብዙ ነገሮች ሲጠሩ ካዩ በኋላ፡ አብዛኛውን ጊዜ ወደ መድረኩ ከመድረሳቸው በፊት ንስሐ ገብተው፡ ዝግጁ ይሆናሉ፡ ምክንያቱም ለሰዎች ብዙ አስከፊ ነገሮች፡ የመሳሰሉትም፡ በመድረኩ ላይ ተነግረዋልና። እናንተም የእነዚያ ነገሮች ምስክሮች ናችሁ።

75 አሁን፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቂት ቃላት ማንበብ እፈልጋለሁ፡ ስለዚህ... ቃሎቼ ይወድቃሉ፡ ሰው ነኝ፡**እነዚህ** ቃላት ግን አይወድቁም፥ **ይህ** የእግዚአብሔር ቃል ነው፡ ሊወድቅ አይችልም።

76 አሁን፡ እዚህ ውስጥ በኢየሱስ ላይ እምነት ያላችሁ ስንቶቻችሁ ናችሁ? እጆቻችሁን እንያቸው። ኦህ፡ ድንቅ ነው! መልካም። እርሱ ዛሬ ትናንትና ሁሌም እንደነበረው ዛሬም ያው እንደሆነ የምታምኑ ስንቶቻችሁ ናችሁ? ኦህ፡ ጥሩ ነው። እኔ የምፈልገው... አሁን፡ ያ እምነታችሁ ነው። ስለዚህ ዛሬ ማታ ሌላ ምን

እንዲኖራችሁ እንደምፈልግ ላሳያችሁ እፈልጋለሁ። የቅዱስ ያዕቆብ 2ኛ ምዕራፍ 14ኛው ቁጥር፡ እስከ 26ኛው ድረስም እነባለሁ። አሁን ምንባቡን በደንብ ተከታተሉ፥

**ወንድሞቼ ሆይ፡ እምነት** አለኝ የሚል፡ **ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር፡** ምን **ይጠቅመዋል? እምነትስ ሊያድነው ይችላልን?**

አይችልም። እግዚአብሔር እንደሚያድንህ የምታምን ከሆነ፡ ማመንና እሱ እንዳደረገው መመስከር አለብህ፡ ከመምጣቱ በፊት... ከዚያም ጽድቅን ያደርጋል፡ አያችሁ።

**ወንድም ወይም እህት ራቁታቸውን ቢሆኑ፡ እ—እና የዕለት ምግብ ቢያጡ፡**

**ከእናንተም አንዱ፡ በሰላም ሂዱ፡ እሳት ሙቁ ጥገቡም ቢላቸው፥ ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን... ባትሰጧቸው፥** ምን **ይጠቅማል?**

**እንደዚሁም እምነት፡ ሥራ** ከሌለው፡ **በራሱ፡ የሞተ** ነው።

**አዎ፡ አንድ ሰው፡ አንተ እምነት አለህ፡ እኔም ሥራ አለኝ፥ እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ፡ እምነቴንም በሥራዬ አሳይሃለሁ ይላል።**

አንተ ታምናለህ... አንድ እግዚአብሔር እንዳለ፥ **አንተም መልካም** ታምናለህ፥ **አጋንንትም ደግሞ ያምናሉ፡ ይንቀጠቀጡማል።**

**ዳሩ ግን አንተ ከንቱ ሰው ሆይ፡ እምነት ያለ ሥራ የሞተ መሆኑን፡ ልታውቅ ትወዳለህን?**

ምን... **አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ላይ ባቀረበ ጊዜ፡ በሥራ አልጸደቀምን?**

**እምነት ከሥራው ጋር አብሮ... ይሠራ እንደ ነበረ፡ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ አያችሁ?**

**መጽሐፍም፡ አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፡ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት ያለው ተፈጸመ፥ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ።**

**እንግዲህ ሰው በሥራ እንዲጸድቅ፡ በእምነት ብቻም እንዳይደለ አያችሁ።**

**እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ፡ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ፡ በሥራ አልጸደቀችምን?**

አሁን የመጨረሻውን ቁጥር፡ በጥሞና አዳምጡኝ፥

**ከመንፈስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ ሁሉ፡ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።**

77 አሁን፡ ሁላችሁም እምነት ያላችሁ፡ በሥራ ላይ ለማዋል የምትፈሩ ከሆነ፡ ምንም አይጠቅምም። ከእምነት የተለየውን ነገር ሁሉ ለምን፡ ለምን አታስወግዱትም? እመኑ ባመናችሁት ነገር ደግሞ ተራመዱ፡ በ—በሚሰሟችሁ ስሜቶች ሳይሆን፡ ወይም ስሜቶች በሚናገሩት ነገሮች ላይ

ሳይሆን፡ እምነታችሁ በሚመሰክረው ላይ። ልክ ነው? በእግዚአብሔር ላይ እምነት አላችሁ፡ እንግዲህ በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንዳላችሁ አድርጋችሁ ተንቀሳቀሱ።

78 አብርሃምም፡ "በእግዚአብሔር እምነት አለኝ፡" ቢል፡ ነገር ግን ልጁን ይስሐቅን ለማቅረብ ቢፈራ፡ እምነቱ ከንቱ ነበር። ጳውሎስ አብርሃምን በእምነት ጸደቀ፡ ጳውሎስ እግዚአብሔር በአብርሃም ባየው ነገር ላይ ተናገረ፥ ያዕቆብ ግን በሥራ አጸደቀው፡ ያዕቆብ ይናገር የነበረው ሰው በአብርሃም ውስጥ ሰላየው ነው። አያችሁ? እግዚአብሔር እምነታችሁን ያያል፡ ሰው ሥራችሁን ያያል። እምነት አለኝ ብላችሁ ወደ ፊት ለመራመድና በሥራ ለመግለጽ የምትፈሩ ከሆነ፡ ምንም አይጠቅምም፡ ፈጽሞ ምንም አይጠቅማችሁም። ማመን አለባችሁ፡ መቀበል አለባችሁ፡ እንደዚሁም እርምጃ መውሰድ አለባችሁ፡ አይደል?

79 እንግዲህ፡ ያ መልአክ ወደ እኔ በመጣ ጊዜ ለመምጣት ለእኔ ቀላል ነገር እንደነበረ ታሰባላችሁ፡ እስከማውቀው ድረስ፡ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ፡ እንደዚያ ያለ ምንም ነገር፡ ፈጽሞ ተከስቶ አያውቅም። በሺዎች ፊት እንድወጣ፡ እና አንዳንድ ጊዜ እስከ ሃያ-አምስት እና ሠላሳ ሺህ የሚደርሱ ሰዎች ፊት እንድወጣ እነ **ሉክ፡ ላይፍ፡ ታይምስ፡ ኮሊየርስ**፡ ተቺዎች... ዶክተሮች ሁሉ ነገር እንዲት ስህተት ለማግኘት እየሞከሩ ባሉበት፡ በእንዲህ ባለ፡ ሰብሰባ ውስጥ፡ እንደዚያ ዓይነት ተግዳሮት ማድረግ? ያ ቀላል እንደነበር ታሰባላችሁ? ዳሩ ግን ወንድምና እህት፡ እግዚአብሔርን አምናለሁ፡ ልክ የነገረኝን አምናለሁ፡ እንደዚያውም ይሆናል።

80 ቆሜ የአገሪቱ ነገሥታትና ገዢዎች እንድጸልይላቸው ይጠሩኛል ያልኩትም፡ ያ... እንደዚያ ብሎ ሰለነገረኝ አምኜዋለሁ። በዓለም ላይ ያለው ታላቁ ንጉሥ ሄጄ እንድጸልይለት የቴሌግራም መልእክት ላከልኝ፡ የእንግሊዙ ንጉሥ ጆርጅ፡ እና የመሳሰሉ የተለያዩ ሰዎች፡ በሀገሪቱም ሁሉ ያሉ ታላላቅ ሰዎች።

81 እዚህ፡ ለረጅም ጊዜ ክራንቾችን ይጠቀም የነበረ፡ አንድ ታላቅ ሰው እዚህ ተቀምጦ ነበር፡ የዩናይትድ ስቴትስ ኮንግረስ አባል የሆነው፡ እዚህ ተቀምጦ ያለው ሚስተር አፕሾው፡ ለብዙ ዓመታት፡ ለሰልሳ-ሰድሰት ዓመታት፡ ጉዳት ደርሶበት፡ ሽባ ሆኖ ነበር። ዛሬ ግን ያለ ክራንቾቹ፡ ያለ ወንበሩ፡ ያለ ምንም ነገር፡ ልክ እንደ ጤነኛ ሰው እየተራመደ እዚህ ይገኛል። መንፈስ ቅዱስ እውነት ነው። እግዚአብሔር ያደርጋል... እጆቹን ወደ ላይ ያነሳው እርሱ ነው፡ ከእናንተ መካከል አንዳንዶቻችሁ አይታችሁት የማታውቁ ከሆነ፡ ይህ እርሱ ነው። ኮንግረሰማን አፕሾውን፡ የኮንግረስ አባሉን አይታችሁ... አይታችሁት የማታውቁ ሰንቶቻችሁ ናችሁ? እጆቻችሁን ስታነሱ እንያቸው። እንግዲህ፡ ለሰልሳ-ሰድሰት ዓመታት የአካል ጉዳተኛ ነበረ፡ ወድቆ ነበር። እና እዚህ መድረክ ላይ ቆሜ፡ ወደ መድረክ ሰወጣ... በሕይወቴ ውስጥ ሰውየውን አይቼው ወይም ሰምቼው እንደማላውቅ፡ እንደማላውቀውም፡ ፈራጁ የሆነው፡ የዘላለም አምላክ ያውቃል። ያልተማረ ሰው ነኝ፡ ምንም ዓይነት ትምህርት ቢኖረኝ ኖሮ፡ ይህን ሰው አውቀው ነበር፡ በቤተ መጻሕፍት ውስጥ ብሆን መጻሕፍትንም ባነብ ኖሮ፡ እንዲሁም... በ1926 ላይ፡ ለፕሬዚዳንትነት የተወዳደረ፡ ይመስለኛል። እርሱም... ከጆርጂያ የመጣ ታላቅ ሰው ነው፡ ሆኖም ፈጽሞ አላውቀውም ነበር።

82 አንድ ምሽትም፡ እዚህ መድረኩ ላይ ወጣሁ፡ ሚስተር ባክስተር መድረኩን

ለቆ ወርዶ ነበር፡ ተመለከትኩ፡ እነሆ ዋይት ሃውስን፡ እዚህ ላይ ወለል ብሎ አየሁት፡ ስለ እርሱም ሁሉን አየሁ፡ መናገር ጀመርኩ፡ ማወቅም አልቻልኩም፡ ለሚስተር ባክስተርም ነገርኩት። ከጥቂት ጊዜያት በኋላ፡ አሁንም ወረደ ስውንየውም ተቀምጦ የነበረበትን አየሁ፡ እርሱ እንደሆነ አየሁ፡ ገና ትንሽ ልጅ ሳለ ጉዳት ሲደርስበት አየሁ። ለዚህ ሁሉ ጊዜም ሽባ ነበረ... ልሄድም ስጀምር፡ የእግዚአብሔር መንፈስ መውረድ ጀመረ፡ አንዲት ሴትም ከዊልቼር ላይ ተነሳች፡ መንፈስ ቅዱስ ለእነርሱ ሲገልጥላቸው ሌሎችም ተጨማሪ ነገሮች ተከሰተው ነበር፡ ልጀምርም ስል፡ እዚህ ያለው ሚስተር ኮፕ፡ ማለትም፡ ወንድም ኮፕ፡ ፓስተሩ ወደዚያ ሮጠ፡ እኔም፡ "ሂድና እግዚአብሔር እንደፈወሰው ለኮንግረሱ ንገረው። ሲሄድ አይቼዋለሁ፡" አልኩት።

83 እዚህ እሱ... ሕዝቡ ሊያዩዋት እንዲችል፡ ኮንግረሰማን፡ እባኮ ይቁሙ? ይኸው፡ ለሰልሳ-ሰድሰት ዓመታት ሽባ የነበረው ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ የኮንግረስ አባል ይህ ነው። "ጌታ ይባረክ፡" እንበል። ጌታ ይባርክህ፡ ወንድሜ።

84 "ስለ እርሱም ምንም ክፋ መናገር አልቻሉም፡ ለአርባ ዓመታት በደጅ ተኝቶ የነበረው ሰው ከእነርሱ ጋር ቆሞ ነበርና፡" ይህ ሰው ደግሞ ለሰልሳ-ሰድሰት ዓመታት የአካል ጉዳተኛ ነበረ። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው...

85 ሚስተር አፕሾው እንዴት... ? በሕይወቴ አይቼው አላውቅም፡ ስለ እርሱ ምንም አላውቅም ነበር፡ የኮንግረስ አባል እንደሆነ ማንንስ እንደሆነ እንዴት አወቅሁ? ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ እዚህ መድረክ ላይ ገልጦታል። አያችሁ? ገልጦታል። የእርሱ... ምስጢሮቹን ያሳውቃል... አሁን፡ ይህ ከእኔ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። አያችሁ? የተወለድኩት ለዚያ ዓላማ ብቻ መሆኑ ነው። አያችሁ? ልክ እንደ ቤተሳይዳ መጠመቂያ ውሃ፡ "እንዴት ያለ ታላቅ ውሃ እንደሆንኩ ተመልከቱ፡" ሊል አይችልም ነበር። መልአኩ ከውሃው ላይ በወጣ ጊዜ፡ ዝም ብሎ ውሃ ነበረና። ልክ ነው? በትክክል።

86 አሁን፡ በእግዚአብሔር ጸጋ፡ እኔ ወንድማችሁ ብቻ ነኝ፡ የጌታ መልአክ ሲወርድ ግን፡ ያን ጊዜ ለእናንተ የእግዚአብሔር ድምፅ ነኝ። ምናልባት ያንን በማለቴ ቅር አሰኛቸችሁ ከሆነ፡ ይቅር በሉኝ፡ እኔም፡ ቅር ሊያሰኝ እንደሚችል ተሰምቶኝ ነበርና፡ ዳሩ ግን፡ እኔ ለእናንተ የእግዚአብሔር ድምፅ ነኝ። አያችሁ? ደግሜ እለዋለሁ፡ ያ ጊዜ በመንፈስ መሪነት ሥር ነበረ፡ አያችሁ፡ በመጀመሪያ ጊዜም እ—እኔ በመናገሬ መጥፎ ስሜት ተሰምቶኝ ነበር፡ ዳሩ ግን ደገመው። አሁን ተመልከቱ፡ እኔ ከራሴ ምንም ማለት አልችልም፡ ነገር ግን እሱ የሚያሳየኝን ነገር፡ እናገራለሁ። ታምኑታላችሁ፡ ምን እንደሚከሰትም ታያላችሁ። አያችሁ፡ **እርሱ** አለ።

87 ጥሩ ስብሰባዎችን ካዘጋጀን በኋላ... አሁን እዚህ ጋር ተመልከቱ፡ ሚስተር አፕሻው እዚህ በሚስተር ፍሪማን ስብከት ሥር ተቀምጦ ነበር። ሚስተር ፍሪማን፡ ኦህ፡ ማይ፡ እርሱ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ኃያል ሰው የሚባል ነው። ወንድም ፍሪማንን የማውቀው ፎቶውን ብቻ በማየቴ ነው፡ እንጂ አላውቀም ነበር። ድንቅ የእግዚአብሔር ሰው እንደሆነ ግን፡ ጥርጥር የለውም። እና ኦራል ሮበርትስ፡ አቤት፡ እሱ... ኦራልን አውቀዋለሁ፡ እና ኦራል ድንቅ የእግዚአብሔር ሰው፡ ታላቅ ሰባኪ እንደሆነ አውቃለሁ። ወንድም ኦጊልቪ፡

ሁለት ጊዜ አግኝቼዋለሁ፡ ድንቅ ሰው። ወንድም አፕሾውም እዚያ ተቀምጦ፡ እነዚያ ሰዎች ይጸልዩለት ነበር። ነገር ግን ምን ሆነ? ልክ ወቅቱ ነበረ። ከዚያም ሲመጣ፡ እና ከ—ከተፈጥሮ በላይ የሆነውን እንቅስቃሴ ተመለከተ... አያችሁ? አይደንቅም ወይ? እግዚአብሔር ቃሉን ይልካል፡ ከዚያም ያንን መልሶ የሚያረጋግጥ ነገር ይልካል፡ አያችሁ። ስለዚህ፡ ሁሉንም አለን፡ ለዚያም የሚያመሰግኑ መሆን አለብን፡ አይመስላችሁም ወይ?

88 አሁን፡ በምስክርነቱ ውስጥ፡ የጌታ ቃል በእኔ በኩል ይናገር እንደነበረ... እሱ እንዳመነ ተናግሯል። ስለዚህ ክራንቾቹና ነገሮቹ ወደ ታች ወደቁ፡ እርሱም በሰላም፡ ጤነኛ ሆኖ ሄደ። አያችሁ?

89 መጀመሪያ ላይ፡ እግዚአብሔር እንደነገረኝ ባላውቅ ኖሮ፡ ለዚያ ሰው አልነግረውም ነበር። አያችሁ? በትክክል። በቻልኩት መጠንም ከሁሉም ጋር ታማኝ ለመሆን እሞክራለሁ። እኔም... እንግዲህ... ኢየሱስም፡ "በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድር የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል" ብሏል። አሁንም፡ አብ ሲፈቅድልን ይህን ማድረግ እንችላለን። አሁን፡ ጌታ ኢየሱስ ይባርካችሁ።

90 አሁንም፡ እዚህ ለሆናችሁ ለእንዳንዶቻችሁ እንግዶች፡ እዚህ የሚገኘው፡ የጌታ መንፈስ፡ በዚህ በጉባኤው፡ ታዲያስ፡ ወይም—ወይም ዛሬ ማታ ወይም በሰልፉ ውስጥ ባሉት ለማንም ሰው፡ ምንም ነገር ባያገኝ ወይም ባይናገር፡ በእነዚህ ሰዎች በኩል እውነት መሆኑ፡ ቀድሞውኑ፡ የጸና—ነው፡ ምክንያቱም ዛሬ ማታ... በየቀኑ... ዛሬ ገና... ደስተኛ ሆኜ ለመቆየት፡ እና—እና ለመጸለይ፡ ታውቃላችሁ፡ እና—እና ወዲያና ወዲህ ለመራመድ፡ ለመደሰትም ብቻ ሞክሬያለሁ። በቅባቱ ሥር ስሆን፡ እቀንሳለሁ... በዚያ ቅባት ሥር በ—በ—በምትሆኑ ጊዜ በአማካይ በቀን ወደ ሁለት ፓውንድ ገደማ እየቀነስኩ ነው። በዚህ ስብሰባ ውስጥ ከቆየሁ ጊዜ ጀምሮ፡ ሰድስት ፓውንድ ይመስለኛል፡ ወይንም እንደዚያ የሚሆን፡ ቀንሻለሁ፡ ብዬ አምናለሁ። ስለዚህ፡ ዛሬ ራሴን ለማዝናናት፡ እና ዝም ብዬ ለመውጣት ሞክሬያለሁ። በእኔ ላይ የሚያደርገው፡ ሰዋዊው የሆነው ክፍል የሚያስወግድ የሆነ ነገር ነው፡ ስለዚህ እንደዚህ ባለ ሁኔታ ረጅም ጊዜ መኖር እንደማይችሉ እናውቃለን። እና አሁን እናንተ ጸልዩ፡ እኔም እጸልያለሁ፡ ከዚያም ሕዝቡን ለጸሎት መስመር ስናሰልፍ፡ እግዚአብሔር፡ ጸሎትን እንደሚሰማና እንደሚመልስ፡ እርግጠኛ ነኝ።

አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

91 የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ እጅግ አመሰግናለሁ በዚህ የክርስቲያኖች ወገን ውስጥ የመቆጠር መብት ማግኘት፡ በዚህ በዳነው የእግዚአብሔር ሕዝብ፡ ከበሽታና ከመከራ ሁሉ አልፈው፡ ከከዋክብት የደስታ ክልል በላይ ከሚያልፉ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች መካከል የመቆጠር ዕድል በማግኘቴ፡ ዛሬ ማታ፡ እጅግ አመሰግናለሁ። ጌታ ሆይ፡ በክርስቶስ ጸጋ፡ ወንድማቸው እንድሆን፡ ስለጠራኸኝ፡ እጅግ አመሰግናለሁ። እጅግ አመሰግናለሁ!

92 አሁንም፡ ውድ አባት ሆይ፡ ከመጀመሪያ ጀምሮ ለሕዝቡ ይህን ያህል ስለመሰከርክላቸው፡ እና ምስኪኑ ያልተማረው አገልጋይህ፡ እንዲናገር የፈቀድክለት ነገሮች፡ ይህም፡ ይናገር የነበረው፡ ምስኪኑ፡ ያልተማረው ሰው

ሳይሆን አንተ እንደነበርክ በማሳየትህ እጅግ አመሰጋኝ ነኝ፡ ያንን ወደ ፍጻሜ ስላመጣኸው ይህም የምድር ታላላቅ ሰዎችና ነገሥታት... አሁንም ተጨማሪ እየመጣ እንደሆነ አምናለሁ።

93 አሁንም፡ አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ እዚህ ካሊፎርኒያ ውስጥ ትልቅ አገልግሎት በሚካሄድበት ቦታ መገኘቴ መታደል ነው። ባርያህ፡ ወንድም ፍሪማን፡ እዚያ ማዶ ላይ ይገኛል፡ እርሱ የት እንዳለ ታውቃለህ አንተ ከእርሱ ጋር ነህና። ዛሬ ማታ እዚያ ብዙዎችን እንድትፈውስ እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ ይሁንልን፡ ብዙዎቹ ምስኪኖች፡ ብዙዎቹ ጥቁር ወዳጆቻችን እዚያ ውስጥ አሉ። አምላክ ሆይ፡ እንድትባርካቸው እና ዛሬ ማታ እንድትፈውሳቸው እጸልያለሁ፡ ታላቅ ምሽት ይሁን። በዚያ በቴምፕልም ደግሞ እንደሰማነው፡ በዚያም... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]... አገልጋይህ፡ ወይዘሮ ማክፈርሰን... [በቴፑ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]... ዛሬ ማታ ነፃ ለመውጣት የሚመጡትን እነዚያን ምስኪን የታመሙ ሰዎችን እያንዳንዳቸውን ዳሰሳቸው... [በቴፑ ላይ ባዶ ቦታ አለ።] ጌታ ሆይ፡ ይሁንልን።

94 በዓለም ዙሪያም፡ ዛሬ ማታ ልጆችህን ሁሉ አሰባቸው፡ አባት ሆይ፡ ፈውሳቸው። እያንዳንዱን አገልጋይና እያንዳንዷን አገልጋዮችህን፡ እና በዚህ ታላቅ የመከር መስክ ውስጥ ለአንተ የሆነ ነገር ለማድረግ ጥረት—ለማድረግ የሚሞክሩትን ሁሉ ባርካቸው። ሁላቸውንም ባርካቸው።

95 ይህም፡ አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ በዚህ ታናሽ መንጋ ውስጥ አሰበን፡ ብዙዎች እንዲፈወሱ፡ ብዙዎች እንዲድኑ፡ ጌታ ሆይ፡ ብዙዎችም በአንተ መገኘት እንዲያምኑ እንጸልያለን። እኛም ሁላችንም፡ ከአገልጋይህ ጋር፡ ከአገልጋዮችህ ጋር፡ እዚህም ያለነው ሁላችንም፡ ከገባንበት ጊዜ ይልቅ የተሻልን ክርስቲያኖች ሆነን በአንተ ላይ የላቀ እምነት ኖሮን፡ ደግሞም ለአንተ የላቀ ፍቅር ኖሮን፡ ዛሬ ማታ ከዚህ ቤት ደጃፍ እንድንወጣ ይሁን፡ አባት ሆይ። እነዚህን የመሳሰሉ በረከቶች፡ ይሁንልን።

96 ዛሬ ማታም የአንተ መለኮታዊ ፈቃድ ቢሆን፡ ጌታ ሆይ፡ ሽባ የሆኑ አንዳንዶች መድረኩን አቋርጠው ቢመጡ፡ ወዲያውኑ በተአምራዊ መልኩ፡ በድንገት፡ ፈውስን ልትሰጣቸው ፈቃድህ ቢሆን፡ እርሱም እንደሆነ አምናለሁ፡ በጉባኤ ውስጥ ያሉ ሰዎች የሚያዩና በታላቅ እምነት የሚያምኑ ሰዎች እንዲሆኑ፡ ጌታ ሆይ፡ እንዲሁ እንዲሆን እጸልያለሁ። ነገር ግን ምንም ቢሆን፡ ካልሆነም፡ ሰንጠይቅህ፡ የለመነነውን እንደምንቀበል እናምናለን። አባት ሆይ፡ ታላቅ እምነትን እንድትሰጣቸው እጸልያለሁ፡ ተስፋ እንዳይቆርጡ፡ ዳሩ ግን በማንኛውም ጊዜ እየጠበቁት፡ በሕይወታቸው ደቂቃዎች ሁሉ በተሻለ ሁኔታ ለመራመድ፡ ከዚህ ደስተኞች ሆነው፡ እየተደሰቱ፡ ወይም—ለማየት፡ ወይም ችግራቸው ምንም ይሁን ምን ለመሻሻል እየሞከሩ ከዚህ ይሂዱ።

97 በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዲሆኑ ያደረጋቸውን የማናቸውንም የልብ ምሥጢራት መግለጥ መለኮታዊ ፈቃድህ ቢሆን፡ ለትሑት አገልጋይህ ተናገር፡ ጌታ ሆይ። እነሆ፡ የክርስቶስ ደም ከኃጢአቴ ሁሉ እንደሚያነጻኝ፡ ታምኜ ቆሜያለሁ፡ ይህም ዛሬ ማታ ለሕዝብህ ልትናገርበት የምትችልበት ቻነል እንድሆን ነው። በሙሉ የልቤ ቅንነት እንደምጠይቅህ፡ ጸሎቴን ሰማ፡ አባት ሆይ፡ በልጅህ፡ በኢየሱስ ስም። አሜን።

98 አሁን፡ ውድ ክርስቲያን ወዳጆቼ፡ ሁላችሁም ከእኔ ጋር እንድትጸልዩ እፈልጋለሁ። ሁላችሁም፡ ምናልባት ከእናንተ ብዙዎቹ በጸሎት መስመር ውስጥ አትሆኑም፡ ደግሞም፡ በጸሎት መስመር ውስጥ መሆን ለሚፈልጉት፥ ብ—ብችል ም—ምኞቴ ነበር። እምነት እየተገነባ ሲሄድ፡ ምናልባት ነገ ማታ፡ መቶ ለመሞከር እንደምንችል፡ አምናለሁ፡ ጌታ ቢፈቅድ። ከዚያም ለመቶ መቀጠል ከቻልን፡ በጣም ብዙ የመለየት አገልግሎት ካልተደረገ፡ ያኔ በሚገባ ላደርገው እችላለሁ፡ አያችሁ። ነገር ግን በ... በ—በዚያ ውስጥ፡ ሲመጣ፡ ብዙ ነገሮች ብቻ አሉ...

99 አሁን፡ እዚያ ጋር ያንን ሙዚቃ መጫወት ሲጀምር፡ ወደ ታች ሲወርድ ሊሰማኝ ሊጀምር ይችላል። ይኸውላችሁ። አያችሁ?

100 ተመልከቱ፡ ክርስቲያን ወዳጆች፡ ከእነዚያ ሥዕሎች... አንዱ የት እንዳለ አላውቅም። ነገር ግን አይታችሁታል፡ ሁላችሁም፡ አይደል? አብዛኞቻችሁ ሥዕሉን አይታችኋል፡ እዚያ ኋላ በጠረጴዛው ላይ አለ። አሜሪካ ባሏት ምርጥ መርማሪዎች በ FBI የእግዚአብሔር መልአክ እንደነበረ፡ በሳይንሳዊው ዓለም ተረጋግጧል።

101 አሁን፡ እርሱ አሁን እዚህ መድረኩ ላይ ይገኛል። በጣም እውነት ነው፡ ውድ ወዳጄ፡ እንዴት እንደምታምን አላውቅም፡ ነገር ግን ያ—ያ እውነት ነው። ወንድማችሁን፡ ሰውዬውን ማየት ከተዋችሁ፡ ዳሩ ግን ስለምናገረው ነገር፡ ስለ ጌታ ኢየሱስ፡ እንዲሁም በመድረኩ ላይ ስላለው ስለ ፈዋሽ መልአኩ የምትመለከቱ ከሆነ...

102 እግዚአብሔር የፈውስ መላእክትን እንደላከ ታምናላችሁ? እንግዲያውስ በናሱ እባብ ላይ የነበረው ምን ነበረ? በቤተሳይዳ መጠመቂያ ውሃ ላይ የነበረው ከሰማይ የወረደ መልአክ ካልነበረ ምን ነበረ። አያችሁ? አያችሁ? የእግዚአብሔር ስጦታ እኔ አይደለሁም፡ የእግዚአብሔር ስጦታ መልአኩ ነው፥ እሱ ከሰማይ ወጣ፡ እኔ ከምድር መጣሁ። እርሱ ደግሞ ምድራዊ ሕዝብን ሊያነጋግር፡ በምድራዊ ዕቃ ሊሸፈን ወይም ሊለብስ ከሰማይ ወደ ታች መጣ፡ አያችሁ፡ ይህም—ይህም በእርሱ... እንድታምኑ፡ በእኔ ላይ ሳይሆን፡ እኔ ስለ እርሱ በምናገረው በእርሱ ላይ፡ ያንን በማድረግም፡ እግዚአብሔር ይፈውሳችኋል።

103 አሁን የጸሎት መስመራችንን እንጥራ። (ምን—ምን—ምን ቁጥሮችን፡ ወይም፡ ፊደላትንና ቁጥሮችን ነው የሰጠኸው፡ ልጄ? ሃምሳ-አንድ እስከ መቶ። ያ ደብዳቤ ምንድን ነው? U። አሁንም U ላይ ነው።) እሺ። ኀምሳ-አንድ እስከ መቶ። አሁን እስቲ እንየው፡ ስንት... ? እስቲ እንየው፡ ይህ ሃምሳ-አንድ ነው፡ የጸሎት ካርድ ነው? እስኪ ማን ነው ይነሣ፡ የጸሎት ካርድ ሃምሳ-አንድ የያዘ፡ እጅህ ብቻ አንሣ። እዚያ ማዶ፡ የጸሎት ካርድ፡ ሃምሳ-አንድ? ሃምሳ-ሁለት እዚህ አለ? እሺ። ሃምሳ-ሶስት እዚህ አለ? አሁን፡ የምትመጡት በ—በዚህ መንገድ ነው። አሁን፡ እነሱን የምናመጣበት መንገድ ይ—ይህ ነው። አሁን፡ እኔ የምችለው...

104 ከፈለጋችሁ፡ እነዚያን ሰዎች ወደዚህ ወደ ላይ ልናመጣቸው እንችላለን፡ እግዚአብሔርም ምን ችግር እንዳለባቸው በትክክል ይነግራል፡ ወይም

ከአድማጮች መካከል አንዱን፡ ወይም የጸሎት ካርድ የሌለውን ሰው ልጠራ እችላለሁ፡ ቅባቱ እዚህ አለ፡ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት አሁን ለመፈወስ እዚህ አለ።

አሁን፡ ስንት... ? አሁን፡ ጥሯቸው... እስቲ እንይ፡ ስንት ናቸው እዚህ ያሉት... ? ለምን፡ መላውን ቡድን በአንድ ጊዜ ልንጠራው እንችላለን።

105 ሁላችሁም እምነት አላችሁ። አሁን አስታውሱ፡ የምትመጡት እናንተ፡ ልክ እዚህ ጋር ትሆናላችሁ፡ እዚህ ስታልፉ ደግሞ፡ እንደምትፈወሱ እመኑ። የተቀራችሁት ደግሞ፡ ለጥቂት ጊዜ ተቀመጡ። እዚያ—አልጋ ላይ ያለሽው ሴት፡ አንቺስ፡ የጸሎት ካርድ አለሽ፡ እህቴ፡ ይዘሻል? እህ?

106 አንድ አፍታ፡ ልጄ አሁን እንደነገረኝ... አሁን፡ በጸሎት መስመር ውስጥ የምትጠሩት በአልጋዎችና በዊልቼሮች በመሳሰሉትም ላይ ያላችሁት፡ ቁጥራችሁን ስንጠራ... ልክ እዚህ ታች ከተሰለፋችሁ፡ ወርጄ እጸልይላችኋለሁ፡ መምጣት ካልፈለጋችሁ ወደ መድረክ ማምጣት እንኳ እያስፈልጋችሁም፡ ወይም ሊያነሷችሁ ከፈለጉ...

እዚህ ያለችው ትንሿ እመቤት እ—እ... ወንበር ላይ የተቀመጠች መሰለኝ።

107 አሁን ሃምሳ-ሦስት፡ ሃምሳ-አራት፡ ሃምሳ-አምስት፡ ሃምሳ-ስድስት፡ ሃምሳ-ሰባት፡ ሃምሳ-ስምንት፡ ሃምሳ-ዘጠኝ፡ ስድሳ። በ—በቁጥር ቅደም ተከተል፡ ልክ ባላችሁበት ሁኔታ በዚህ በኩል ተሰለፉ። በጣም ጥሩ። እሺ፡ ስድሳ። ያ ማለት... ?

108 መልካም፡ አንዴ ጠብቁኝ፡ የሆነ ቦታ ላይ የሆነ የተሳሳተ ነገር ያለ ይመስለኛል። ኦህ፡ የሆነ ሰው ነው የሚያመጣው... ትንሿ ልጅ፡ እሷ ናት... ? አንድ አፍታ ጠብቁ። የሆነ ሰው ወደዚያ ሊያመጣት ነው? ምስኪን ነገር እዚያው አስቀምጧት። የጸሎት ካርድ አለሽ፡ የኔ ማር? እንዲጸለይልሽ መብት አለሽ። አንድ አፍታ ጠብቁ፡ እዚያው ወንበር ላይ እንድትቀመጥ ተዉአት።

109 ስለዚህ ነገር ምን ታስቢያለሽ፡ የኔ ውድ? ይህ እውነት እንደሆነ ታምኛለሽ? አሁን በአንቺ ላይ እየመጣ ያለው ያ እንግዳ ስሜት ምን እንደሆነ ታስቢያለሽ? ያ መንፈስ ቅዱስ ነው፡ አይደለም እንዴ? ያንን ታምኛለሽ፡ ታምኛለሽ፡ የኔ ማር? ወንድም ብራንሃም የተናገረው እውነት እንደሆነ፡ የእግዚአብሔር መልአክ እነዚህን ነገሮች እንዳውቅ እንደላከኝ ታምኛለሽ? ያንን ታምኛለሽ? አንቺ—ሽባ እንደሆንሽ ወይም የሆነ ነገር እንደሆንሽ አያለሁ፡ አንድ እግርሽ እንደተቆረጠ አምናለሁ። ልክ ነው? ልክ ነው? አዎን፡ እኔ... አላውቅሽም፡ አውቅሻለሁ እንዴ፡ የኔ ማር?

110 አንድ ወንድም፡ እዚያ ውስጥ ሲራመድ፡ አያችሁ፡ የራእዩን ዓይነት፡ አቋረጠው። አሁን አንድ ደቂቃ ብቻ፡ አሁን ሁሉም ሰው በድጋሚ ትሑታን ሁኑ።

111 አሁን እንደገና ወደዚህ መንገድ ተመልከቺ፡ የኔ ማር፡ ልገናኝሽ ብቻ ነው የምፈልገው። አያችሁ፡ ብዙ ሰዎች ማመን እየሞከሩ ነው፡ ያ... አሁን፡ አዎን፡ ኧ-ህ። አንቺ... አንቺ... ይህን ያደረገው ካንሰር ነው፡ አይደለም እንዴ፡ የኔ ማር? ወሰደው... እግርሽን ቆረጡት። አሁንም በሰውነትሽ ውስጥ አለ፡ አሁንም እየተሰራጨ ነው። ልክ አይደለም እንዴ? አሁን ልጸልይልሽ ነው፡ የኔ ማር።

112 የሰማይ አባታችን፡ እዚያ ተቀምጣ ያለችውን ያችን ምስኪን ትንሽ ልጅ፡ በሕይወት እንድትኖር እንደምትፈቅድላት አምናለሁ፡ ውድ እግዚአብሔር ሆይ። ለልጅቷ ምሕረት አድርግላት፡ ውቧ፡ ትንሿ ነገር። ፈውሷን አሁኑኑ ሰጣት። በእግዚአብሔር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እጸልያለሁ። አሜን።

113 እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ የኔ ማር። አሁን ደህና እንደምትሆኚ ታምኛለሽ? ታምኛለሽ? አሁን ትቀበይዋለሽ? እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ ጥሩ ነው። ነሽ። በትክክል፡ እርሱ አግኝቶሻል።

[ወንድም ቢሊ ፖል፡ "አባዬ? " አለ—እርታዒ።]

(ኧ-ሀ? )

["ከእነዚያ ሁሉ ሰዎች፡ እና የመጡት ወደ ሃያ የሚጠጉ ሰዎች ብቻ ናቸው። ሁሉም፡ ሀ፡ ከሃምሳ-አንድ፡ እስከ መቶ፡ እያንዳንዳቸው።"]

(ምን አልክ? )

["ሀ እፈልጋለሁ፡ ሃምሳ-አንድ እስከ መቶ፡ የተገኙት ግን ወደ ሃያ ብቻ።"]

(ኦህ። ኦህ፡ መልካም።)

114 ከሃምሳ-አንድ እስከ መቶ፡ ተሰለፉ፡ ከሃምሳ-አንድ እስከ መቶ፡ በዚያ በኩል ተሰለፉ። ሁሉም ሰው በተቻለ መጠን በትህትና ሁኑ፡ በሙሉ ልባችሁ እመኑ።

115 ምን ነበር፡ ጌታዬ? [አንድ ወንድም ስለ ትንሿ ልጅ ካርድ አስተያየት ሰጠ—እርታዒ።] ኦህ፡ አዎን። ያ አይፈውሰም፡ ብቻ... ነገር ግን በሙሉ ልቤ አምናለሁ... ማየት አልቻልኩም፡ ሰዎቹ በጣም ይንቀሳቀሱ ስለነበር። ወደ ልጅቷ ይበልጥ ልጠጋ ነው ከ... አምናለሁ እኔ... ምን... ? ሰትፈወሱ፡ ነጭ ብርሃን አያለሁ። ያው ብርሃን በዙሪያው ሄዶ ይባርካል፡ ልክ እንደ በረከት ነው፡ አየዋለሁ። ህጻኗ ልጅ ደህና እንደምትሆን አምናለሁ። ደህና እንደሆነች አምናለሁ፡ እህቴ። አያችሁ? ምንም የሚያስጨንቅሽ ነገር እንደሌለ አምናለሁ፡ ውዴ፡ ትድኛለሽ።

116 እሺ። አሁን፡ ሁሉም ሰው... አሁን፡ እነሱ ምናልባት፡ ጥቂት... አሁን፡ አስተናጋጆቹ በቁጥር ቅደም ተከተል መምጣታቸውን ያረጋግጣሉ፡ ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች እንዴት እንደሚሆኑ አላውቅምና። እኔ ብቻ—ብቻ... ጌታ እንደሚመራው።

117 አሁን፡ ሁሉም ሰው አሁን ጸጥ ይበል። አሁን፡ ከኋላ ያላችሁ፡ ሁላችሁም በጸሎት መስመር፡ እዚያ ኋላ በጸሎት መስመር ውስጥ ያላችሁ ሰንቶቻችሁ ናችሁ በሙሉ ልባችሁ—እናንተ—እንደምትድኑ የምታምኑት? እንደምትድኑ፡ በሙሉ ልባችሁ እመኑት። አሁን ራሳችሁን ለጌታ ኢየሱስ አሳልፋችሁ በመስጠት፡ እንዲህ በሉት፡ "አሁን፡ የሰማይ አባቴ ሆይ፡ እንደ ፈዋሼ አድርጌ እቀበልሃለሁ። ዛሬ ማታም በጸጋህ፡ ምንም ቢፈጠር፡ በዚያ የጸሎት መስመር ውስጥ ስመጣ፡ በረከቶችህን እቀበላለሁ። እጆችም በእኔ ላይ ሲጫኑ እንደምድን አምናለሁ። ከእንግዲህ ወዲህ ፈጽሞ አሉታዊ ምስክርነት አይኖረኝም፡ ጌታን አምናለሁ"? እጃችሁን ከፍ አድርጋችሁ፡ "ይሄን አምናለሁ፡ አሁን ተናዝዣለሁ፡" ትላላችሁ? እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

118 አሁን፡ አንድ ሰው አንድ ጊዜ እንዲህ አለኝ፡ ለእኔ ሳይሆን፡ ለሌላ ወንድም፡ አንድ—አንድ አገልጋይ ተች አጠቃውና፡ "ኦህ፡ አሳፋሪ ነው! ምንም ነገር ከመከሰቱ በፊት ሄደው እንዲያምኑ ለሰዎቹ ይነግራቸዋል፡" አለው።

119 በእምነት ካልሆነ በስተቀር እንዴት ልትፈወሱ ነው? አብርሃም ከሣራ ልጅ እንዲያገኝ እንደሚፈቅድለት እግዚአብሔርን አመነ፡ ዳሩ ግን ለሃያ-አምስት ዓመታት ፈጽሞ አልተከሰተም፡ እርሱም እንደሚሆን በማመን ሁልጊዜም እየበረታ ሄደ። እኛም የአብርሃም ልጆች ነን። ልክ ነው?

120 መልካም። አሁን ሁሉም ሰው በተቻለ መጠን በመንፈስ ይሁን። አሁን፡ ምናልባት መንፈስ ቅዱስ... ለአንድ አፍታ ብቻ። አሁን፡ ምናልባት ለተወሰነ ጊዜ፡ በጥልቅ ቅብዓት እስክገባ ድረስ ት—ትንሽ መለየት ብቻ ይሰጠኝ ይሆናል፡ እና—እና ከዚያም... ይህም ሰዎቹም ማለፍ እንዲችሉ። እነርሱም ቢመጡና፡ ልክ ወደ ውሃው መጠመቂያ እንደሚገቡ ቢያምኑ፡ እኔ የጌታ መልአክ እዚህ መድረኩ ላይ እንዳለ፡ እርሱም እንደሚያደርገው አምናለሁ።

አሁን እንጸልይ።

121 አባት ሆይ፡ አንተ ሁሉንም ነገር ታውቃለህ፡ እኔ ምንም አላውቅም። ነገር ግን እኛ—አሁን በታላቅ ጉብኝት እንድትመጣ ሕዝብህንም እንድትባርክ፡ ለእነርሱም እንድትናገር፡ ጌታ ሆይ፡ አሁኑኑ፡ እንድትፈውሳቸውም እንጸልያለን። አንተም እዚህ እንዳለህና፡ አገልጋይህም ጋር እንዳለህ... መተረኪያን ሰጥ። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ። እያንዳንዱም ይፈወስ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን። አሜን።

እሺ፡ አሁን በጸሎት ውስጥ ሁኑ። እናንተም ከፈለጋችሁ...

122 አሁን፡ አምጡ፡ በሽተኛችሁን አምጡ። አንድ አፍታ ጠብቁ። አሁን፡ በትክክል ምን እንደሆነ እኔ አላውቅም። እንደምን አለሽ፡ እመቤት? ይህንን ወደ ላይ ከፍ ያደረግሁት በመሰመሩ የሚያልፉት በሽተኞች፡ ታውቃላችሁ፡ ለምን፡ እነርሱ—እነርሱ—ለመስማት እንዲችሉ፡ ማለቴ እዚያ ያሉት ሰዎች በሽተኛውን እንዲሰሙ፡ አያችሁ፡ እንደዚያ ማለቴ ነው። አንቺም ቢሆን፡ እንዲጸለይልሽ መጥተሻል። ምናልባትም፡ ስለ ራስሽ፡ ትንሽ ነገር ለማወቅ ፈልገሻል፡ ምክንያቱም እ—እኔ—ልታውቂው የምትፈልጊው ነገር እንዳለ፡ ይሰማኛል፡ ይህም ሁ—ሁኔታዎችሽ ነው።

123 ተጨንቀሻል፡ አይደለም እንዴ? እጅግ በጣም ተጨንቀሻል። በጣም ብዙ ክብደትም፡ ቀንሰሽ የለም እንዴ? ከአንቺ በጣም የምትከብድ አንዲት ሴት በፊቴ ቆማ አያለሁ። ደግሞም፡ ልበል፡ አንቺ አገልጋይ አይደለሽም ወይ፡ ወይም በቃሉ ውስጥ እንደዚያ ያለ ነገር አይደለሽም እንዴ? ታስተምሪያለሽ፡ ወይም እንደዚያ ያለ ነገር? አዎ፡ የሆንሽው ያ እንደሆነ አሰቤ ነበር። ኧ-ህ። አሁንስ ታምኛለሽ? ሁልጊዜ በጣም ተወጣጥረሻል። ነገሩ ምን መሰለሽ፡ ራስሽን በውጥረት ውስጥ ከትተሸዋል፥ ያም ሆነ ይህ፡ በብዙ ውጥረት ውስጥ አልፈሻል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መጨነቅ ጀምረሻል፡ ልክ በጣም እንድትወጣጠሪ ያደረገሽ፡ የሆነ ነገር እንደተፈጠረብሽ ይመስላል። እንግዲህ፡ ያ ሊያደናቅፍሽ ከሚሞክር ከዲያብሎስ ሌላ አይደለም፡ ስለዚህ፡ ይህ ሊረግምሽና ያንን በፊትሽ ሊጥል የሚሞክር ሰይጣን ነው። እናም እ... አንቺ ልትቀበዪው አይገባም፡ እሱን ወደዚያ

ጣይው እ—እና አሁን ማመን አለብሽ። ያ እውነት ነውን? እንግዲህ፡ ለጥቂት ጊዜ ወደዚህ ነይ።

124 አባት ሆይ፡ ስለ ምሕረትህና ስለ መልካምነትህ አመሰግንሃለሁ፡ አሁን ውድ እህታችንን እንድትፈውስ እጸልያለሁ።

125 አንተ ጋኔን፡ ሴቲቱን ልቀቃት፡ ከውስጧ ልቀቅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ልቀቃት!

126 አሁን እዚ ተመልከቺ፡ እኅቴ ሆይ፡ አሁን ተቀበይው? መልካም። እየተደሰትሽና ደስተኛ ሆነሽ ሂጂ፡ ወደ ጌታም ሥራ ግቢ።

127 አሁን፡ "ጌታ ይባረክ፡" እንበል። ሴትዮዋ—ሴትዮዋ ደህና ልትሆን ነው፡ ደህና ትሆናለች።

128 አሁን አንድ አፍታ ጠብቁ። አሁን፡ እዚህ በጎኔ ሌላ ሰው ቆሟል። አሁን ሁሉም ሰው...

129 ወደዚህ ና፡ ወዳጄ። [ያ ወንድም፡ "ጌታዬ፡ ችግሬ ምንድነው" አለ?—እርታዒ።] ወዳጄ? ["ጌታዬ፡ ችግሬ ምንድነው?"] እንግዲህ፡ በዚህ በኩል ብትመለከተኝና እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ ብታምነኝ... በርግጥ፡ በዚህ የህይወት ጉዞ ውስጥ እኔና—አንተ እንግዳሞች ነን፡ አንተ እዚያ ከመቆምህ በቀር፡ እኔ—አንተን አላውቅህም፡ ወንድሜ። አንተ ወደዚህ ላይ ስትወጣ፡ ደስ የሚል መንፈስ እንዳለ ተገንዝቤያለሁ። አንተም፡ እየተሰቃየህ ነው። በትክክል። እና አንተ—የጨጓራ ችግር አለብህ፡ አይደለም እንዴ? አዎ፡ ጌታዬ፡ ያ ትክክል ነው፡ እየተሰቃየህ ነው። ምግብ ወደ አንተ ሲመጣና ከዚያም ሲርቅ አያለሁ፡ ስለዚህ አውቃለሁ። ደግሞም ልበልህ፡ አንተስ፡ አገልጋይ አይደለህምን? አንተም፡ የወንጌል አገልጋይ ነህ። ይህ ልክ አይደለምን? አዎ፡ ጌታዬ። እንዲሁም—አንተ—እማኝ ነህ፡ አይደል፡ ወንድሜ? መፈወስም ትፈልጋለህ፡ አትፈልግም? እስቲ ለአንድ ደቂቃ ወደዚህ ቅረብ፡ ወንድሜ።

130 ሰማያዊ አባታችን ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ እጄን በባሪያህ ላይ አኖራለሁ። መጽሐፍ ቅዱስም እነርሱም በታመሙ ሰዎች ላይ እጃቸውን ቢጭኑ ይፈወሳሉ ብሏል።

131 አንተ ሰይጣን፡ ይህን ሰው ልቀቀው፡ ልታስረው እየሞከርክ ነው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ሰውነየውን ልቀቀው!

132 አሁን፡ ወንድሜ፡ የጨጓራ ችግርህን ያመጣው ልክ አሁን እንዳለፈችው ሴት ዓይነት ተመሳሳይ ነገር ነው፡ የጭንቀት ሁኔታ ነው። ረዘም ላለ ጊዜ ተጨንቀህ ነበር፡ በቅርቡም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ተባብሷል። ልክ አይደለም እንዴ? አዎ ጌታዬ። ከዚያም ይህን ያስከተለ፡ ብዙ ችግርና የመሳሰሉት ነበሩህ። አሁን፡ ቀጥል ሂድ... እውነትን ነግሬሃለሁ። ልክ ነው? አንተ አገልጋይ ነህ። ያ እውነት ከሆነ እጅህን ወደ ላይ አንሳ። ይ—ይህ እውነት ነው። እሺ። አሁን እ... እኔ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ካልሆነ በስተቀር፡ ያንን የማውቅበት ምንም መንገድ የለም። ልክ ነው? አሁን፡ እየተሰማህ ነው፡ አንተ—የወንጌል አገልጋይ እንደመሆንህ መጠን፡ ልክ እዚህ ጋር የሆነ እንግዳ ነገር እንዳለ ይሰማሃል፡ ወይም፡ የ—የፍቅር ስሜት፡ እና... ልክ ነው? አሁን፡ ሰዎቹ ያ ትክክል መሆኑን እንዲያዩ፡ እጅህን አንሳ። አዎን።

133 አሁን፡ ይህ አገልጋይ ምስክር የሆነላት፡ ለእርሱ የተናገረው ያ የጌታ መልአክ ነው። እንግዲህ፡ ከዚህ ከጌታ መንፈስ የበለጠ፡ ምን አለ? እኔ ስለ ሰውነየው ምንም እንደማላውቅ በሰማይ ያለው እግዚአብሔር ያውቃል ከ... ዳሩ ግን አሁን እዚህ መድረኩ ላይ ቆሜ፡ ወደ ላይ ሲወጣ፡ ደስ የሚል መንፈስ ተሰማኝ። “አንተ ክርስቲያን አማኝ ነህ፡” አልኩት። አሁን፡ በጌታችን በኩል ለናትናኤል የተናገረው ያው መንፈስ ይህ ነው፡ “እነሆ በእውነት እስራኤላዊ የሆነ፡ አማኝ፡ በእርሱም ዘንድ... ”

እርሱም፡ “ከወዴት ታውቀኛለህ” አለው?

134 እዚህ ደግሞ፡ ችግሩን፡ ነገሮቹንና የጨጓራ ሁኔታውን፡ የመሳሰሉትንም፡ አየሁት፡ ያም ትክክል ነበረ፡ እርሱ የመንፈስን ምስክርነት ይሰማል። ይህስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻዎቹ ቀናት እንደሚሆኑ ተስፋ የሰጠን ያው መንፈስ አይደለምን?

135 እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። ሂድ ጤነኛ ሰውም ትሆናለህ። እግዚአብሔርም ይባርክህ፡ እና እ...

እስኪ ሁላችንም፡ “ጌታ ይመስገን፡” እንበል፡ የሚያምኑትን ሁሉ ለመፈወስ እግዚአብሔር እዚህ እንዳለ በሙሉ ልባችሁ እመኑ።

136 እሺ፡ እስቲ ነይ፡ እህቴ። እዚያ ወንበር ላይ ተቀምጠሽ እንደተፈወስሽ ብነግርሽ ምን ትያለሽ? ተፈውሰሻል፡ እህቴ። መንገድሽን ቀጥዪ እየተደሰትሽም ተፈውሰሽ ሂጂ። አሜን።

137 አሁን፡ አድማጮች ሊረዱት ይችሉ ዘንድ፡ አንዳንድ ሰዎች... አንዳች የጸሎት ካርድ የሌላችሁ የሆናችሁ ወደዚህ እንድትመለከቱ እፈልጋለሁ፡ እንድታምኑ እፈልጋለሁ።

138 እዚያ ጋር ያለፈችው እህት በስኳር በሽታና በመሳሰሉት ስትሰቃይ የነበረችው፡ አሁን ደህና ትሆናለች፡ የደም ማነስ።

139 አሁን፡ እምነት ብቻ ይኑርሽ። አሁን ቆይ፡ አንዲት ሴት እዚህ ቃሬዛ ላይ ሆኖ እኔን እየተመለከተችኝ ነው። አሁን፡ እመቤት፡ አንቺን በማነጋገር ብቻ አንቺን መንካት እፈልጋለሁ። የጸሎት ካርድ የለሽም፡ እንግዳ ነሽና፡ እኔ አላውቅሽም፡ ነገር ግን አርትራይተስ አለብሽ። ልክ አይደለም ወይ? ደግሞም፡ አቅም አልባ አድርጎሻልም። ልክ አይደለም ወይ? አሁንም፡ በሙሉ ልብሽ ካመንሽ፡ የእግዚአብሔር ተአምራት፡ ወይም፡ ነገሮች በመድረኩ ላይ መከሰት ሲጀምሩ፡ በአንቺ ቦታ ብሆን ኖሮ፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፡ አሁን እቀበልሃለሁ፡” እንደምለው አምናለሁ። እዚህ በዊልቼር ላይ የተቀመጠችውን ሴትዮ አቋርጦ የሚሰብ አንድ ሰው እዚህ አለ ምን እየተካሄደ እንዳለ ማየት አልችልም። ነገር ግን—በሙሉ ልብሽ እርሱን ብቻ ከተቀበልሽ፡ እግዚአብሔር እንደሚፈታሽ፡ ተነስተሽም ከሕንፃው ወጥተሽ ጤነኛ ሰው መሆን እንደምትችይ አምናለሁ። አሁን ያንን አስቢበት። እምነት እንዲኖርሽ እየሞከርሽ ነው፡ አይደለም እንዴ? እንዲኖርሽ እየሞከርሽ ነው። በልብሽም፡ ምኞት አለሽ፡ አይደለም እንዴ? ከእግዚአብሔር ጋር፡ የጠበቀ ጉዞ እያለሁ፡ ከእርሱ ጋር የበለጠ ተጠግቶ ለመጓዝ፡ ያንንም በላይሽ ላይ አያለሁ፡ ጥላ የሚመስል ነገር ከላይሽ ላይ ስህበት ያደርጋል።

140 ሌላ ሰው አሁን እ... አሁን አንድ አፍታ ብቻ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ እየተንቀሳቀሰ ነው። ልክ የተቀመጠችው ሴትዮ ይመስለኛል፡ ወይም፡ ሰውየው፡ ማናቸውም ቢሆኑ፡ ልክ እዚህ ጋር፡ አይ፡ እዚያ ወንበር ላይ ያለችው ሴት ትመስለኛለች። የሆነ ችግር አለ፡ ደም ነው፡ አይደለም እንዴ፡ እህቴ? አኒሚያ ወይም የሆነ ነገር-... አዎ፡ ልክ እዚያ ላይ። ልክ አይደለም እንዴ? በእግርሽ ቁሚ። ኢየሱስ ክርስቶስ ጤነኛ ያደርግሻል። ያ... አሜን። ልክ ሴትዮዋ... አዎ።

141 ልክ ከእሷ ጀርባ ደግሞ፡ ሌላ አለ። በትክክል። ቁሚ፡ እመቤት። በትክክል። እነሆ ልታገግሚ ነው።

142 አሁን እንዴ ቆይ፡ ሴትዮዋ፡ እዚያ አጠገብሽ የተቀመጠችው ጓደኛሽ፡ የካንሰር ታማሚ ናት፡ መልካም፡ በይ ቁሚ፡ እህቴ። ካመንሽ ብቻ ጌታ ኢየሱስ ከዚያ ካንሰር ይፈውስሻል። አሜን።

አሁን ሁሉም ሰው በቻለው መጠን በመንፈስ ይሁን። መልካም፡ ልጄ፡ ሴትዮዋን አምጣት።

143 እህት ሆይ፡ አማኝ ነሽ? መንፈስ ቅዱስ አሁን እዚህ እንዳለ ታምኛለሽን? የሚሰማሽ እሱ እንደሆነ ታምኛለሽ? እህቴ ሆይ፡ እነሆ ስለ ፈውስሽ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እ—እባርክሻለሁ። ሂጂና ደህና ሁኚ። እግዚአብሔር ይባርክሽ።

አሁን እምነት ይኑራችሁ፡ እያንዳንዳችሁ በሙሉ ልባችሁ እመኑ።

144 አሁን፡ አንቺ ታናሽ እህቴ፡ ዛሬ ከሰዓት በኋላ ስለዚህ ጉዳይ ምን እየተሰማሽ ነው? አማኝ ነሽ? እግዚአብሔር—ይህን ለአንቺ እንዳደርግ እንደላከኝ ታምኛለሽ? አንቺ—በእውነት በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽ? ታምኛለሽ። ስለ አንቺ ምንም ሳላውቅ፡ ምን ችግር እንዳለብሽ ልነግርሽ ብችል፡ ምን ታስቢያለሽ? ድንቅ ይሆናል፡ አይደል? አሁን ተመልከቺ፡ ስለዚህ ይህን እርግጠኛ ሆነሽ እንድታውቂ፡ ለተወሰነ ጊዜ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ቆይተሻል፡ አይደለም እንዴ? በትክክል፡ ከልጅነትሽ ጀምሮ። እርግጥ ነው አሁን፡ ለዚህም መንስኤ የሆነው፡ በዓይንሽ ላይ ያለው አስቲግማቲዝም ነው፡ ዓይኖችሽ ጥሩ የማየት ችሎታ የላቸውም። ያ በአንቺ ላይ ካሉት ችግሮች አንዱ ነው፡ ያ ብቻ አይደለም። ከዚያም ደግሞ፡ አንቺ... እግዚአብሔርን ለማገልገል በሞከርሽበት መንገድ ራስሽን ፈጽሞ እንዳላረካሽ—እያለሁ፡ መንገድሽን የሚከተል ጥላ ስለማይ፡ ሁልጊዜም ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ የሆነ ጉዞ ትፈልጊ ነበር። አንቺም በልብ ህመም እየተሰቃየሽ ነው፡ (ትክክል አይደለም? )፡ ያም፡ ያሰጨንቅሻል። ትክክል አይደለም? አሁን፡ ይህ ለምሳሌ... ? እውነት ነው አይደል? እውነቱን ነግሬሻለሁን?

145 አሁን፡ ቃሌን እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ ትቀበዪዋለሽ? ያ ከሆነ... በሕይወትሽ ውስጥ የነበረውን ካወቅሁ፡ በሕይወትሽ ውስጥ የሚሆነውን አውቄአለሁን? አሁን በእግዚአብሔር ፊት እርሱን እንደ ፈዋሽሽ አድርገሽ እንደምትቀበዪውና፡ ራስሽን ቀና አድርገሽ እንደምትሄጂ፡ እየተደሰትሽ፡ እና እግዚአብሔርን እያመሰገንሽ፡ በቻልሽው መጠን ከእርሱ ጋር ተጠግተሽ እንደምትኖሪ፡ ጤነኛ ሴትም እንደምትሆኚ ትናገሪያለሽ? ያንን ማድረግ ትፈልጊያለሽ? ነይ ወደ ፊት ቅረቢ።

146 የሰማይ አባታችን፡ ይህችን ወጣት እባርካታለሁ፡ አቤቱ ነገሮችን ሁሉ አስወግድ። ጌታ ሆይ፡ እዚያ ግብ ላይ ለመድረስ፡ እየሞከረች፡ ወደዚያ አጥብቃ እየገፋች ነው። ሰይጣን ያለ ጊዜዋ ወደ መቃብር ሊልካት ቆርጦ ተነስቷል፡ አንተ ግን ልትፈውሳት እዚህ አለህ። ጌታ ሆይ፡ ይህ የልብ ችግር ከእሷ እንዲወጣ፡ እባርካታለሁ፡ እ—እንዲሁም መልካም ሴት ትሆናለች። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

147 አሁን፡ እመኚ። በጣም ጥሩ። መነጽርሽን አውልቀሽ፡ ከመድረኩ ወርደሽ ጤነኛ ልትሆኚ ትችያለሽ፡ እህቴ። እግዚአብሔር ይባርክሽ።

እስቲ ሁላችንም፡ "ጌታ ይመስገን፡" እንበል።

148 መልካም። አሁን፡ የመሰማት ችሎታዋ ነው። አሁን፡ በአንቺ ላይ ያንን አያለሁ... ዓይኖችሽ በጣም ተጎድተዋል፡ እየታወርሽ ነው። እግዚአብሔር ጤናማ እንደሚያደርግሽ ታምኛለሽ? በሙሉ ልብሽ?

149 አያችሁ፡ አንድ ሰው እዚያ ቆሞ ነበር፡ ከዚያም አቋረጠኝ። ወደዚያ ከመግባቷ ጥቂት ቀደም ብሎ ያዝኳት። የማየው ነገር...

150 አሁን፡ ዕይታሽን እያጣሽ ነው። አንቺ እናት፡ ኢየሱስ ክርስቶስም ማያሽን ሊሰጥሽ እዚህ አለ። ያንን ታምኛለሽ? በሙሉ ልብሽ? አሁን፡ እናት፡ ምናልባት ዕድሜሽ ትንሽ ገፋ ያለ ሊሆን ይችላል፡ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ይወድሻል። እጅሽን ሰይዝ፡ ዛሬ ማታ እቤቴ ሰለ እኔ እየጸለየች ያለችውን የራሴን ውድ እናቴን አስባለሁ፥ በየምሽቱ እንደዚያ ታደርጋለች። እናም አሁንም ካለሽ መ—መዳን ውጪ፡ በእናቶች ቀን ልትቀበዪው የምትችዪው፡ ከሁሉ የላቀው ስጦታ፡ በጥሩ ሁኔታ ለማየትና፡ እንደገና ለመንቀሳቀስ መቻልሽ ይሆናል። ያ ድንቅ አይሆንም? እንግዲህ፡ እናቴ ሆይ፡ ከ—ከእነዚህ ቀናት ውስጥ አንዱ አንቺና እኔ በጌታችን በኢየሱስ ፊት መቆማችን እንደማይቀር አውቃለሁ። አሁን፡ እንዲፈውሰሽ ልጠይቀው ነው፡ አንቺም ሰለ እርሱ የነገርኩሽ እውነት እንደሆነ አምነሻል። እንግዲያውስ ራስሽን እንድታጎነብሺ እፈልጋለሁ።

151 አባቴ ሆይ፡ ይህች ውድ እናት እያለቀሰችና፡ ዕውር ሆና፡ ራሰዋን በትከሻዬ ላይ እንዳስደገፈች፡ ሰይጣን ይህን ክፉ ነገር አድርጎባታል፡ በዓይኖቿ ውስጥ ያሉት ነርቮች መሥራት አቁመዋል፡ እሷም ዕውር ሆናለች። ዳሩ ግን አባት ሆይ፡ የአይን ብርሃን ልትመልስላት አንተ እዚህ አለህ። ዛሬ ማታ በጣም በትህትና እና ታዛዥ ሆና ቆማለች፡ የጥንቷ ሳራን እያሰብኩ ነው፡ በሩ ላይ ሰለነበረው ዕውር በርጤሜዎስ እያሰብኩ ነው፡ በጭቃ ላይ የተፋህለትና ዓይኖቹን የቀባኸው ሰው አስባለሁ። አሁንም፡ አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ በሥጋ አካል በመካከላችን ተቀምጠህ ቢሆን ኖሮ፡ ሮጣ፡ ራሰዋን በትከሻህ ላይ ታስደግፍ ነበር፡ ውድ አባት ሆይ፡ ትባርካት ነበር። እኔም በጣም ደካማ ምትክ እንደሆንኩ... አውቃለሁ፡ ዳሩ ግን፡ ውድ እግዚአብሔር ሆይ፡ አንተ ከእኛ ጽድቅን የምትፈልግ ብትሆን ኖሮ፡ የት በተገኘ? ስለዚህ አባት ሆይ፡ እንደገና የአይን ብርሃን ትሰጣት ዘንድ፡ እባርካታለሁ። በልጅህ በኢየሱስ ስም፡ ይህ የዕውርነት መንፈስ ይህችን አሮጊት እናት ይልቀቃት፡ አሁንም ማየት እንድትችል ይሁን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

152 አሁን፡ እናቴ፡ እዚህ ወደ እኔ እንድትመለከቺ እፈልጋለሁ። እታይሻለሁ? በደንብ ታይኛለሽ? ይህን እንድታውቂ ብቻ፡ ጣትሽን በአፍንጫዬ ላይ

እንድታደርጊ እፈልጋለሁ... ጣቶቼን ማየት ትችያለሽ? [ያቺ እህት፡ "ለማንኛውም፡ በከፊል ላየው እችላለሁ"አለች። አርታዒ።] እንግዲህ፡ ጣቶቼን አሁን ማየት ቻልሽ? ["ኡህ፡ አዎን።"] ልታያቸው ትችያለሽ? ሰንቱን ቀሰሬአለሁ? ["አንድ።"] እሺ፡ አሁንስ ስንት ነው? ["ሁለት።"] ይኸው እንግዲህ፡ እናቴ፡ ማየት ሆኖልሻል።

153 የሆነው ነገር ምንድነው፡ ሰይጣን፡ የዕውርነት መንፈስ... እንዲሁም፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ "ደንቆር እና ዲዳ መንፈስ" ብሏል... አሁን፡ ሐኪሙ ሊል የሚችለው—የጆሮሽ ታምቡር እንደሞተ፡ ወይም ዓይኖችሽ እንደጠፉ፡ ነርቮቹ፡ ታውቂያለሽ። ነገር ግን አዳምጪ። ነገሩ ምን መሰለሽ፡ እርሱ የሚለው ብቸኛው ነገር፡ ነርቩ ሞቷል ነው። እንዲሞት ያደረገው ግን ምንድን ነው? ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ የያዘው ነገር ነበረ፡ በሰውነትሽ ሁሉ ላይ አልሞተም፡ እዚያ ላይ ብቻ ነው የሞተው። ጥሩ። አሁን፡ በእጄ ዙሪያ ስስ ፕላስተር ቢጠመጠም፡ **እንደዚያም** አድርጎ ቢይዘው፡ ዝውውሩን ይዘጋዋል። አያችሁ? እንግዲያውስ፡ በጣቶቼ ላይ የምቀባው ቅባት ሁሉ ምንም አይጠቅመውም፡ መደረግ ያለበት ነገር ተፈጥሮ እንደገና ዝውውር እንዲያደርግ ይህን ማላላት ነው። ልክ ነው? እንግዲህ፡ የ—የእይታ፡ የዓይን ነርቭ ኃይል፡ በዓይንሽ ውስጥ አይፈስም ነበር ምክንያቱም ከተፈጥሮ በላይ የሆነ አካል፡ ጋኔን፡ የዕውርነት መንፈስ ነርቭሽን ይዞት ስለነበር ነው። አየሽ? አሁን ሄዷል፡ በተሻለ ሁኔታ ማየት የቻልሽበት ምክንያት ያ ነው።

154 ደህና ትሆኚያለሽ። አሁን በጥሩ ሁኔታ ማየት ችለሻል፡ አይደል? አያችሁ... ? አሁን በደንብ ይታየኛል ብላለች። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እናቴ። እየተደሰትሽና እግዚአብሔርን እያመሰገንሽ፡ በራስሽ ከመድረኩ ውረጂ። እስኪ "እግዚአብሔር ይመስገን፡" እንበል።

155 እንደምን አለሽ፡ እህቴ? ነይ ወደ ፊት ቅረቢ። አንቺም፡ ዓይኖችሽ መፈወስ ትፈልጊያለሽ፡ አይደል። እግዚአብሔርን ታምኚያለሽ? ሙሉ በሙሉ ዕውር ልትሆን የደረሰችውን ያቺን ሴት፡ እንዲሁም ትናንት ማታ ሙሉ በሙሉ ዕውር ለነበረችው ማዳን ከቻለ፡ ለአንቺም ዓይንሽን ሊሰጥሽ አይችልም እንዴ፡ እህቴ? አሁን፡ እንድታደርጊ የምፈልገው አሁን በአቅራቢያ ያለው ይህ ነገር አንቺን ለመባረክ እንደሆነ እንድታምኚ ነው። አሁን፡ እግዚአብሔር እንደሚያደርገው በፍጹም ልብሽ ብታምኚ፡ ልክ ወደ አንቺ ወርዶ ይፈውስሻል፡ ይባርክሻልም፡ ያንንም ከአንቺ ላይ ያሰወግደዋል። ዓይኖችሽ—እየደከሙ፡ ያለማቋረጥ እየባሰባቸው ነው። ልክ አይደለም እንዴ? ያው ተመሳሳይ ነገር ነው፡ እየዘጋው ያለው፡ የዲያብሎስ ኃይል ነው፡ እህቴ... ሐኪሞች ስለ ጉዳዩ ከዚህ በላይ ምንም ሊያደርጉ አይችሉም፡ ምክንያቱም፡ አየሽ፡ አ—አብቅቶለታል፡ እርሱም እንኳ እንደዚያ ብሏል። አሁን፡ ያ ሲሆን... እዚያ ጋር ነርቩን፡ የዓይን ነርቩን እየዘጋው ብቻ ነው፡ ኃይሉ ከእንግዲህ ወዲህ በእርሱ ውስጥ አይፈስም።

156 አሁን፡ ነርቩ የተዘጋው በእጅሽ ላይ፡ ወይም—ወይም በሌላ በየትኛውም ቦታ አይደለም፡ ያለው በዓይንሽ ውስጥ ነው፥ በጆሮሽ ውስጥ ቢሆንኖሮ፡ ያኔ መስማት አትችይም ነበር። አሁን፡ ሐኪሙ ነርቩ ሞቷል ሊል ይችላል፡ እርግጥ ነው እርሱ የሚሠራው በአምስቱ የስሜት ሕዋሳት ላይ ብቻ ነው። ዳሩ ግን ኢየሱስ ያለው፡ "ዲዳው መንፈስ ከሰውየው በወጣ ጊዜ፡" መስማት የተሳነው

መንፈስ። “የዕውርነት መንፈስ ከሰውየው በወጣ ጊዜ።” አየሽ? ይህ... እርሱ መንፈስ ነው፡ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ።

157 አሁን፡ ያንን መንፈስ ከአንቺ ላይ አውጥቶ የሚጥለውን የእምነት ጸሎት እንድጸልይልሽና እንድትድኚ በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን መሠረት፡ ወደዚህ እንደተላክሁ ታምኚያለሽ? ነይ ወደ ፊት ቅረቢ፡ እህቴ።

158 እግዚአብሔር ሆይ፡ ሳሰበው፡ በመንገድ ላይ በእጇ ውስጥ ልትይዘው ያለውን ነጭ ምርኩዝ። ሰዓቱ ይህ ነው። እግዚአብሔር ሆይ፡ መፍትሔ አሳጥተው እንደመለሷትና ምንም ሊደረግላት እንደማይችል እዚያ ራእይ አይቻለሁ፡ አንተ ግን ልትፈውሳት ትችላለህ።

159 ሰይጣን፡ ሴትዮዋን ልቀቃት፡ አንተ የዕውርነት መንፈስ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ከእሷ ውጣ! አሜን።

160 አሁን ታምኚያለሽ? እንግዲያውስ፡ መነጽርሽን አውልቂና ሂጂ። ኧ-ህ።

ይኸው ያለ መነጽሯ ሄደች። እሷም... በጣም ጥሩ። ሁሉም ሰው አሁን ወደፊት ይቅረብ፥ ሁላችሁም አሁን በሙሉ ልባችሁ እመኑ።

161 እንደምን አለሽ፡ እህቴ? አንቺም፡ መነጽር አድርገሽ አያለሁ። አዎ፡ እመቤት። አሁን፡ እኛ... አሁን፡ ወደ እኔ—እንድትመለከቺ እፈልጋለሁ። አሁን፡ እኔ እና አንቺ እንግዶች ነን፡ አይደለንም እንዴ፡ እህቴ? ለሌላ አይደለም... ችግርሽ ምን እንደሆነ ማየት እስክችል ድረስ ብቻ ነው፡ ከዚያ በኋላ ቀጥታ እንቀጥላለን። አሁን፡ መንፈስሽን ለ—ለ—ለማግኘት ብቻ ነው የማነጋግርሽ። አይ፡ ነገር ግን የፈለግሽው ስለ ዓይኖችሽ አይደለም። አርትራይተስ አለብሽ፡ አይደለም እንዴ? ልክ አይደለም ወይ? በጣም ጥሩ። ለአንድ አፍታ ወደዚህ እንድትመጪ እፈልጋለሁ።

162 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ ሰይጣን እህታችንን አስሯታል፡ አንተ ግን ልታድናት እዚህ አለህ።

163 አንተ ሰይጣን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ከሴትዮዋ ውጣ፡ ፍታት!

164 አሁን፡ እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ ትታዘዢኛለሽ? በጌታ በኢየሱስ ስም፡ እጆችሽን ወደ ላይ አንሺ፡ እግሮችሽን **እንደዚህ** ወደ ላይና ወደ ታች አንቀሳቅሺ። አርትራይተሱ ጠፍቷል፡ አንቺ... አሜን። አሁን፡ እዚህ ጋር... ? ...

165 ከአርትራይተስ የተነሳ ከእንግዲህ ወዲህ አትታሰርም፡ እግዚአብሔር ከዚያ ፈውሷታል። ያ ብቻ አይደለም፡ ነገር ግን አስቲግማቲዝም የነበሩት ዓይኖቿም፡ ተፈውሰዋል፡ ከዓይን በስተጀርባ ያለው ካታራክት፡ ጠፍቷል። አሁን ሁሉም ሰው በመንፈስ ይሁን በሙሉ ልባችሁ እመኑ። በእግዚአብሔር እመኑ፡ እግዚአብሔርም ይፈጸማል።

166 በጣም ጥሩ፡ አሁን ሴትዮዋን አምጧት። እሺ። እንደምን አለሽ፡ እህቴ? እ—አንድ ጋዜጣ እ—እያነበብሽ አየሁሽ፡ ይህም፡ በውስጡ የኮንግረስ አባሉ ምስክርነት ያለበት ነበር። ያ ድንቅ ነበር፡ አይደል፡ እናት? በጣም ጥሩ ነው። አዎን፡ እመቤት። ብዙ ችግር አለብሽ። አይደል? የኩላሊት ችግር ለረጅም ጊዜ ሲያስቸግርሽ ቆይቷል፡ ዕድሜ ያስቆጠረ የሴቶች በሽታና የመሳሰሉት። ደግሞም፡ አርትራይተስ አለብሽ፡ የለብሽም እንዴ፡ እህቴ? ጠዋት ከአልጋ ለመውጣት ስትሞክሪ አያለሁ፡ በሌሉቱ ጊዜ የመገተር ችግር ይገጥምሻል።

ልክ አይደለም እንዴ? በትክክል። እጆችሽን ወደ ላይ አንሺ። ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን ሙሉ ጤና ይሰጥሽዳል፡ እህቴ። አዎን። እግርሽን ወደላይና ወደታች **እንዲህ** እርጊ። አንቀሳቅሺያቸው... አትፍሪ። እግሮችሽን **እንደዚያ** ወደ ላይና ወደ ታች አንቀሳቅሺያቸው። በይ መሻትሽን ውሰጂ... አዎን፡ እናቴ። "ውድ ኢየሱስ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡" እያልሽ ከመድረክ ውረጂ፡ አብቅቷል።

እሰቲ፡ "እግዚአብሔር ይመስገን" እንበል። እህታችን ተፈውሳለች። በትክክል። አሁን ስትመጡ ሁላችሁም በመንፈስ ሁኑ።

(መልካም፡ ለአፍታ ብቻ። ከፈቀዳችሁልኝ፡ በመለየት ጸጋ ጊዜ፡ ይህን አንድ ተጨማሪ ሰው ልጥራ።)

167 ያም ሆነ ይህ፡ እንድለው የፈለግሽው ያንን ነበር። እያሰብሽ ነበር። አሁን፡ አትጨነቂ፡ አየሽ፥ ለተወሰነ ጊዜ በጭንቀት ቆይተሻል። አሁን፡ እህቴ፡ አሁን የሚሰማሽ ይህ ነገር፡ አንቺን የሚጎዳ ምንም ነገር የለውም፡ ሊረዳሽ የሚችል ነገር ነው። አየሽ? ሊረዳሽ የሚችል ነገር ነው፡ የእግዚአብሔር መልአክ ነው። እርግጥ ነው፡ ነ—ነፍስሽን ያስፈራታል።

168 አሁን፡ እጅግ በጣም ተደናግጠሻል፡ አይደለም እንዴ? እንግዲህ ያንን የጀመረሽ ከማረጥ ጊዜሽ ከወጣሽበት ጊዜ ጀምሮ ነው፥ ለተወሰነ ጊዜ በውስጡ ቆይተሻል። ልክ አይደለም እንዴ? በትክክል። በእውነት የድካም ስሜቶች ይመጡብሻል። ልክ ነው አይደል? ሌላው ደግሞ፡ በደምሽ ውስጥ፡ የስኳር በሽታም፡ አለብሽ አይደል? ልክ ነው? በትክክል። በጣም ጥሩ፡ ሲያስቸግርሽ የነበረ የኩላሊት ችግር፡ ያማል፡ ያደክማልም። ሲመሽ፡ ለማረፍ በወንበር ላይ ትቀመጪያለሽ... ልክ አይደለም እንዴ? እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እናቴ። ከመድረኩ ውረጂ፡ በጌታ በኢየሱስ ስምም ጤነኛ ሁኚ።

169 እስኪ፡ "ጌታ ይባረክ" እንበል። በጣም ጥሩ። ሁሉም ሰው በመንፈስ ይሁን። አሁን አንድ ደቂቃ ብቻ። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።]... ? ... አሁን በዚህ በኩል ባለው ህዝብ ላይ፡ ልክ እንደ-ወተት ዓይነት መልክ፡ ልክ ክሬም-መሳይ ነገር በሕንፃው ውስጥ ተንጠልጥሏል። ይህም፡ መንፈስ ቅዱስ ነው። እንደዚሁም—ወዳጆች ሆይ፡ ልክ በሁላችሁም ላይ ነው። እና ካመናችሁት ትፈወሳላችሁ። አሁን፡ ከቻልኩ፡ እግዚአብሔር ቢረዳኝ፡ ለጉባኤው ለመጸለይ እሞክራለሁ።

170 እዚህ በዊልቸር ላይ አንዳንድ ሰዎችን እንዳሉን አይቻለሁ፡ ወርጄ ለእናንተም እጸልያለሁ። (አሁን፡ ወንበሮቹ ላይ ወዳሉት ሰዎች ከመምጣቴ በፊት በጣም እንድደክም አታርጉ።)

171 አሁን፡ አሁን፡ እህቴ፡ እዚያ በትንሿ ቃሬዛ ላይ ሳለሽ፡ እ... ከተቻለኝ፡ አንቺን ለማየት እየሞከርኩ ነው። ምን እንደተፈጠረ አላውቅም፡ ሁለት አሉ... እዚህ መሃል፡ እያችሁ፡ ጋርዶኛል። አሁን፡ በሙሉ ልብሽ ለማመን ሞክሪ።

172 እዚያ በክራንቾች ያለህ አንተም፡ ወንድሜ፡ በወንበሩ ላይ ያለኸው፡ አሁን እምነት ይኑርህ፡ በሙሉ ልብህ እመን።

173 አሁን፡ ስንጸልይ ሁሉም ሰው ለእነዚህ ሰዎች በመጸለይ ታግዙኛላችሁን?

174 አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ ውዷን እህታችንን ባርካት፡ አሁንም ትፈወስ፡ ከዚህ ሕንፃም፡ ጤነኛ ሆና ትውጣ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

175 ከዚያ ወጣ በይ። ወዲህ ነይ፡ ቀጥለሽ ያለሽው አንቺ። እንደምን አለሽ፡ ትንሽ እህቴ። ኦህ፡ ማይ፡ እ... ምንድን ነው... ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ? ችግርሽ ምን እንደሆነ እንድነግርሽ ትፈልጊያለሽ? የአከርካሪ አጥንት መጣመም ነው። አይደል? በጣም ጥሩ።

176 እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህችን ምስኪን ልጅ ባርካት፡ ጤናማም ትሁን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም።

ኦህ! አባት ሆይ፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህችን ትንሽ ልጅ ባርካት። እንድትፈውሳት እና ጤናማ እንድታደርጋት እጸልያለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

ደህና እንደምትሆን ታምኛለሽ?

ነይ፡ እህቴ።

አባት ሆይ፡ እኅታችንን እንድትባርክና፡ ጤናማ እንድታደርጋት እጸልያለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እጠይቃለሁ። አሜን።

እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እኅቴ።

እሺ። ነይ፡ እመቤት።

አባት ሆይ፡ እኔ ሰባርካት እህታችንን እንድትባርክና ጤነኛ እንድታደርጋት እጸልያለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

177 እንደምን አለሽ፡ እህቴ? አዎ። አንቺ—አንቺ እምነት አለሽ፡ አይደል እንዴ? እህቴ፡ አርትራይተሱ ቀድሞውኑ እንደተወሽ፡ ታምኛለሽ።

178 በጣም ጥሩ። አንቺም እንደዚሁ፡ እህቴ። አሁን በሙሉ ልብሽ እያመንሽ፡ ሂጂ፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ተቀበዪው።

179 ሁሉም ሰው በሙሉ ልባችሁ እመኑ። በጣም ጥሩ።

እኔ ብማጸን እንደሚለቀው ታምናላችሁ?

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ትንሹ ልጅ ይፈወስ፡ እናትም፡ ጭምር።

አሁን ሂዱ፡ እነሆ ደህና ሊሆን ነው፡ ችግሩ ሊለቀው ነው፡ እርሱ ጤነኛ ይሆናል።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ስለ እህቴ ፈውስ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እጠይቃለሁ።

እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ ውድ እህቴ።

እኅቴ ሆይ፡ በሙሉ ልብሽ፡ ታምኛለሽ?

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንድትፈውሳት፡ እጠይቃለሁ።

180 አሁን፡ እ... ነይ፡ እህቴ። በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽን? እሺ። ካመንሽ፡ እግዚአብሔር ከልብ ችግርሽ እንድታገግሚ ያደርግሻል።

181 በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ፈውሷን እጠይቃለሁ። አሜን።

182 እምነሃል፡ ወንድሜ?

183 አምላክ ሆይ፡ ስለ አካሉ ፈውስ ወንድሜን እባርከዋለሁ። በእግዚአብሔር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

184 በሙሉ ልብህ፡ ታምናለህ፡ ወንድሜ? አንድ ነገር ሆነ። ይህን ልነግርህ ይገባኛል፡ አየህ፡ ምክንያቱም አንተ—ካልነገርኩህ በ—በስተቀር ከዚህ ልታገግም አትችልም። ከነገርኩህም፡ እንደ እግዚአብሔር ነቢይ ትቀበለኛለህ? አጥብቀህ የያዝከው፡ የማትተወው ነገር አለ (ልክ አይደለም ወይ? )፡ ልትተወው የሚገባህ ልማድ አለህ። በትክክል። ሂድ። እግዚአብሔር ይባርክህ።

እሺ። እኅቴ፡ ታምኛለሽ?

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እኅቴ ሆይ፡ ለፈውስሽ፡ እባርክሻለሁ።

አሁን እያመንሽ ሂጂ፡ ፈውስሽም ታገኚያለሽ።

185 እሺ። እኅቴ፡ ታምኛለሽ? በጣም ብዙ ነገሮች፥ ድካም፡ ያለ ጊዜው ማረጥ፡ አርትራይተስ፡ እንደዚሁም፡ ደግሞ... ልክ ነው አይደል? በጣም መጥፎ ነው። ሂጂና እህቴ፡ በጌታችን በኢየሱስ ስም፡ ተፈወሺ።

እሺ። ነይ፡ ውዷ እህቴ።

የሰማይ አባት ሆይ፡ እህታችንን ባርክ እና አሁን ፈውሳት። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እጠይቃለሁ።

እሺ። እህቴ፡ ታምኛለሽ?

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለፈውስሽ እባርክሻለሁ።

አሁንም፡ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡” እያልሽ፡ ሂጂ።

እሺ። እኅቴ፡ ታምኛለሽ ወይ?

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ አሁን እንዲፈውስሽና፡ ደህና እንዲያደርሽ እጠይቃለሁ።

“ተመስገን፡ ጌታ ሆይ፡” እያልሽ ሂጂ።

186 አሁን፡ ጉባኤው ሆይ፡ ኹህ፡ ሰዎች፡ እናንተ—ከዚህ እንደወጣችሁ ወዲያውኑ እግዚአብሔርን ማመስገን ጀምሩ፡ “ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ። ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡” በሉ። ሁሉም ሰው በመንፈስ ይሁን።

አሁን፡ እኅቴ ሆይ፡ ታምኛለሽ?

በጌታ በኢየሱስ ስም፡ እህታችንን ለክብርህ ፈውሳት። አሜን።

187 እሺ። አሁን፡ እህቴ፡ ስለሱ ምን ታስቢያለሽ? በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽ? አንድ አፍታ ብቻ፡ እዚያ ጋር... የሆነ ማውራት አለ፡ ትንሽ እየረበሸኝ ነው። ለአንድ አፍታ ወደዚህ በኩል ተመልከቺ። በአንቺ ላይ እየሠራ ያለ የሆነ እንግዳ ነገር አያለሁ፡ ያ... ትንሽ ፈርተሻል፡ አይደል እንዴ? አንቺ... እንግዲህ፡ ነገሩ ምን መሰለሽ፡ አሁን ያለሽበት የሕይወትሽ ጊዜ ነው፡ የሴቶች መዛባት አለብሽ። ስለዚህ አሁን፡ ሄደሽ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንድትፈወሺ እፈልጋለሁ። አሜን።

መልካም። እሺ። እኅቴ፡ ታምኛለሽ?

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ስለ ፈውስሽ እጠይቃለሁ። ጌታ ሆይ፡ ይሁንልን።

አሁን በደስታ፡ በደስታ ሂጂ።

188 እሺ። እኅቴ ሆይ፡ ታምኛለሽ? እንደ ቀድሞው መብላት ትፈልጊያለሽ (ልክ አይደለም እንዴ?) እንደገና ጥሩ ጤንነትና ጨዋራ እንዲኖርሽ ትፈልጊያለሽ? እግዚአብሔር ይባርክሽ። ሂጂና ማድረግ እንደምትፈልጊው አድርጊ፡ አሜን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም።

189 በጣም ጥሩ። ከሴቶች ችግር መገላገል፡ አይደለም እንዴ፡ እህቴ፡ ጤነኛም መሆን ትፈልጊያለሽ? ቀጥይ። እግዚአብሔር ይባርክሽ። አሜን።

እስቲ፡ "ጌታ ይባረክ" እንበል። (ከአቅሜ በላይ ሆኖብኛል... )

190 በጣም ጥሩ። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። አሁን የፈለግኸውን ሂድና ብላ፡ አይዞህ በርታ፡ እግዚአብሔርም ሊባርክህና ጤነኛ ሊያደርግህ ነው።

191 መልካም። አሁን ና። እሺ፡ ወንድሜ። በሙሉ ልብህ ካመንህ፡ ጤነኛ ትሆናለህ አይንህም በደንብ ደህና ይሆናል።

192 እግዚአብሔር ወንድማችንን ይባርክ፡ በኢየሱስ ስም።

193 እሺ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ። አሁን ነይ። ጤነኛ መሆን ትፈልጊያለሽ፡ አትፈልጊም እንዴ፡ ከልብ ችግርሽ መገላገል?

194 በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ትፈወሰ።

(ሌሎቻችሁስ ምን ታስባላችሁ? ሁላችሁ... ምን ትላላችሁ? ወደዚያ እንድገባ ትፈልጉኛላችሁ? ሁሉም እነዚህ ናቸው፡ ወይስ ጥቂት የቀሩ አሏችሁ? )

195 አሁን፡ ሰዎቹን በዊልቼሮቹ አድርገዋቸዋል፡ ሊሰለፉ ነው፡ እኔም ወደ ታች እወርዳለሁ፡ ለቀሪዎቹ ለእነዚህ ልጸልይ ነው። እያመሰገናችሁም ቀጥታ እለፉ። የተቀሩትንም አምጡ... ? ... የተቀሩትን በዚያ ሊያሳልፉቸው ነው። በጣም ጥሩ፡ ሴትዮዋን ቀጥታ አምጧት።

ነይ፡ ውዷ እህቴ። በጣም ጥሩ።

የሰማይ አባት ሆይ፡ እኅታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንድትባርክ እና ጤናማ እንድታደርጋት እጸልያለሁ። አሜን።

ያ በእጅሽ ላይ ምን ያህል ጊዜ ቆይቷል... ? ...

196 ነይ፡ እህቴ። እንደ ቀድሞው መብላትና ጤነኛ መሆን አትፈልጊም እንዴ? ችግርሽ ያ እንደነበረ እንዴት ላውቅ እችላለሁ? በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ። ልክ ነው? አሁን ሂጂ፡ በእግዚአብሔር የተባረክሽ ነሽ፡ ደህናም ልትሆኚ ነው፡ እህቴ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ ውዷ እህቴ። አሜን።

197 እሺ፡ እህቴ። ኦህ፡ ብዙ ነገሮች በልብ ህመም እየተሰቃየሽ ነው፡ የልብ ህመም፡ መጥፎ የጭንቀት ችግርም አለብሽ።

198 አምላክ ሆይ፡ እኅታችንን እንድትፈውሰና ጤናማ እንድታደርጋት እጸልያለሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

አዎን፡ ነርቮችሽ እንዲህ ያደረጋቸው ያ ነው... ? ...

199 መልካም። ኦህ፡ ማይ! ውድ ወንድሜ፡ በክራንች ላይ እንደሆንክ አያለሁ። ስለዚህ ነገር ምን ታስባለህ? እውነት እንደሆነ ታምናለህ? ታምናለህ። አሁን፡ ልፈውስህ አ—አልችልም፡ ወንድሜ። ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ነቢይ

ካመነከኝ፡ ምን ችግር እንዳለብህ ለማወቅ እችላለሁ። ያንን በሙሉ ልብህ ታምናለህ? ታምናለህ? አሁን እየተሰማህ ያለው ነገር፡ እና ያ መንፈስ፡ ያ የእግዚአብሔር መልአክ ነው።

200 ችግርህ ለሰው የማይታወቅ ነው። ዝም ብለህ ትደክማለህ፡ አይደለም እንዴ? ዝም ብለህ ትደክማለህ፡ እጅግ ትደክማለህ። እና በዚያ ላይ ትራመዳለህ ለ—ለጥቂት ጊዜ ያህል፡ ከዚያም አቅም ታጣና ትቀመጣለህ። ልክ ነው? በትክክል። እንደዚያ እያደረግህ እንደነበር እንዴት ላውቅ እችላለሁ? የማውቅበት ብቸኛው መንገድ በራእይ በኩል ብቻ ነው፡ ምክንያቱም አላውቅህምና። ልክ ነው? ነገሩ ምን መሰለህ፡ የነርቭ ሥርዓትህ ከአገልግሎት ውጭ ሆኗል፡ ወንድሜ፡ በአከርካሪህ ውስጥ። እስኪ ለአንድ አፍታ ወደዚህ ና።

201 እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህን ሰው ባርከው፡ ብርታትን ስጠው፡ “ደካማው፡ ‘እኔ ብርቱ ነኝ’ ይበል፡” ብለሃልና። ሰባርከው፡ ጌታ ሆይ፡ ይሁንልን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

202 ከመድረኩ ስትወርድ እንዲህ እንድታደርግ እፈልጋለሁ፡ ያረጀውን ክራንችህን ወስደህ እዚያ ታች ጣለውና ቀጥታ ወደ ቤትህ ሂድ... ? ...

203 መልካም። ነይ፡ እኅቴ አሁን ተፈወሺ፡ ከዓይን ችግርሽ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተፈወሺ። አሜን። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ።

እሺ። ታምናለህ፡ ወንድሜ?

በጌታችን በኢየሱስ ስም፡ ወንድሜን ፈውስ። አሜን።

አምነህ ሂድ፡ ወንድሜ።

እኅቴ ሆይ፡ ታምኛለሽ?

በጌታ በኢየሱስ ስም፡ እህቴን ፈውሳት።

እኅቴ ሆይ፡ ታምኛለሽ?

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ፈውስሽን ተቀበይ። አሜን።

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እኅቴ ሆይ፡ ፈውስሽን ተቀበይ።

አሁን በደስታ፡ ሂጂ።

ታምኚዋለሽ እህቴ?

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ፈውስሽን ተቀበይ። አሜን።

204 ጌታ ይመስገን! በጣም ጥሩ፡ ሁላችንም፡ “ጌታ ይባረክ” እንበል። እጆቻችንን ከፍ አድርገን እናመሰግነው። እሺ። አሁን፡ እዚህ ታች በዊልቼሮች ላይ ያሉ ገና ያልደረስንላቸው ሰዎች አሉ። አሁን፡ ሁሉም ሰው ከእኔ ጋር እንዲጸልይ እፈልጋለሁ። እንግዲህ፡ እነዚህ ሰዎች የጸሎት ካርድ የላቸውም፡ እኔ ግን፡ እንዲሁ ልጸልይላቸው እወርዳለሁ፡ ምክንያቱም እነሱ—እዚህ ተቀምጠዋል፥ ከእነርሱ አንዳንዶቹ፡ አንድ ወይም ሁለት የጸሎት ካርድ ያላቸው ይመስለኛል። አብሬያቸውም ልጸልይ እፈልጋለሁ፡ አገልጋይ ወንድሞቼም አብረውኝ እንዲቀላቀሉ እፈልጋለሁ።

205 አሁን፡ ለእያንዳንዳቸው እንዴት እንደተከሰተባቸው፡ ስለ ሁኔታው ሁሉ ልነግራቸው እችላለሁ፡ እናንተን ልፈውስ ግን፡ አልችልም። አንድ ነገር ግን

ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። እኔ ስጸልይላችሁ ጌታዬን ኢየሱስን እንደ ፈዋሻችሁ ትቀበሉታላችሁን? ከአገልጋዮቹ አንዳንዶቹ ከእነርሱ ጋር እዚህ ይሰለፉ፡ ስለዚህ፡ ደግሞም፡ እነርሱ በዚህ ውስጥ ሊ—ሊካፈሉ ይችላሉ፡ ሙሉውን።

206 ጉባኤው በመንፈስ እንዲሆን እፈልጋለሁ። እግዚአብሔር እዚህ ጋር ታላቅ ተአምራት ያድርግ። አሁን፡ የአካል ጉዳተኞችና የተጎዱት ብቻ ናቸው፡ በእውነትም ሸባዎችና የተጎዱ ከመሆናቸው የተነሳ መውጣት አይችሉም። እዚያው ታች እንዲቀመጡ ተዉአቸው። አሁን ሁሉም ሰው በመንፈስ ይሁን። አንዳንዶቹ አገልጋዮች ልክ እዚህ ኋላ ይቁሙ።

207 ክርስቲያን ወዳጆች ሆይ፡ እዚህ ታች ለእነዚህ ሰዎች ሳገለግል ስንቶቻችሁ በጸሎት አብራችሁኝ ትሆናላችሁ? አብራችሁኝ በሙሉ ልባችሁ ታምናላችሁ? በመንፈስ ሆናችሁ እንዲሁም ራሳችሁን አጎንብሳችሁ በጸሎትም ትሆናላችሁ? ጌታችን ኢየሱስ እነዚህን የታመሙትን እንዲፈውስ እየጠየቅነው ነው… እዚህ የተቀመጡት ቤተሰባችሁ ቢሆኑስ፡ ከእነርሱ አንዳንዶቹ ሙሉ በሙሉ የተጣመሙ እ—እና ሸባዎች፡ አንዳንዶቹም ምርኩዝ በእጃቸው የያዙ፡ ሙሉ በሙሉ ዕውሮች? ጌታችን ኢየሱስ እንደሚፈውሳቸው እምናለሁ። አሁን፡ ሁሉም ሰው ይቀመጥ፡ ሁሉም ከሸባዎቹ በስተቀር። አሁን እዚህ ያሉት እንካሶች ብቻ ናቸው።

[ወንድም ሆል ለጉባኤው መመሪያ አስተላለፈ—አርታዒ።]

208 አሁን፡ እዚህ ላላችሁት ሸባ ለሆናችሁት ሙሉ በሙሉ ለተጣመማችሁትና ለተጎዳችሁት፡ እዚህ መድረኩ ላይ ሆኜ በአንዳንዶቹ ሰዎች ላይ በረከቶችን ሳውጅ ስታዩኝ ልቤ ለእናንተ ያዝናል ይራራል። ሙሉ በሙሉ ሸባ ሆነውና ተጣምመው ከነበሩት መካከል እዚህ የነበሩ በርካታ ሰዎች ተፈውሰዋል፥ ያንን ሰምታችኋል። ለምሳሌ፡ ለስልሳ-ስድስት ዓመታት ሸባ የነበረው ሚስተር አፕሾው፡ ከእናንተ መካከል ከትንሽ ልጅነቱ ጀምሮ እርሱ በነበረበት ሁኔታ ውስጥ የነበረ አንድም የለም፡ እርሱ ገና የአሥራ ሰባት ዓመት ልጅ ሳለ የመጀመሪያው የአከርካሪ አጥንቱ በተሰበረ ጊዜ ለመፈወስ ሞክሯል። እሱ ልክ እንደ ሟቹ ፕሬዝዳንታችን፡ ፕሬዝዳንት ሩዝቬልት፡ ከወገቡ እስከ ታች ድረስ እሱን የያዘበት ቦታ ነበር። እኔ የምችለው እግዚአብሔር እንድሠራው የነገረኝን፡ ራእይ ማየትና ስለ ጉዳዩ፡ ምን ሊከሰት እንደሚችል መናገር ብቻ ነው።

209 እርሱ ብቻ ሳይሆን፡ ዛሬ ማታ ከዊልቼሮች ላይ ተነስተው የተፈወሱ ሌሎችም በዊልቼሮች ውስጥ እዚህ ተቀምጠው ነበር፡ ከእናንተ ብዙዎቻችሁ ያንን ታውቃላችሁ። ፊኒክስ ውስጥ፡ ከባለፈው ሳምንት በፊት፡ እግዚአብሔርም እንዴት ከዊልቼር እንዳነሳቸው ታውቃላችሁ።

210 እዚህ ቆሜ ሳለ፡ እያየኋችሁ ነው፡ ምን ችግር እንዳለባችሁ ልነግራችሁ እችል ነበር፡ አንዳንድ ነገሮች ግን… አብዛኛውን ጊዜ በዊልቼር ላይ ላሉት ስናገር፡ አንድ ሰው እንዲህ ሊል ስለሚችል ነው፡ "እንግዲህ፡ ማንም ቢሆን ወደዚያ አይቶ ያ ሰው ሸባ ነበረ።" በትክክል። አገልግሎቴ በዚያ ላይ ብዙ አያተኩርም፡ ጤናማ የሚመስል ሰውን ማየትና ከዚያም ምን ችግር እንዳለበት መንገር ነው፡ አያችሁ፡ ጤነኛ-መልክ ያለው ሰውን፡ እናም ከሆነ… ታስተውሉታላችሁ።

211 ዛሬ ማታም፡ አድማጮች፡ ለእናንተ እንግዶች፡ ወደ ታች ወርጄ ለእነዚህ ሰዎች ለመጸለይ ጥንካሬዬን ለማቆየት ስል በቻልኩት መጠን ወደ ኋላ ለመያዝ ሞክሬያለሁ። አሁን፡ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ ነው፥ እናንተ ሽባዎች እና ሌሎች፡ እውነትን እንደተናገርኩ ታምናላችሁን? ታች ወ—ወርጄ እ—እ—እግዚአብሔር እንዲባርካችሁ፡ እጠይቃለሁ፡ ለእያንዳንዳችሁም እጸልይላችኋለሁ፡ እግዚአብሔርም እንድትድኑ እንደሚፈቅድላችሁ እንድታምኑ እፈልጋለሁ። አሁን፡ አሁኑኑ ሊያደርገው ይችላል። ልትቆሙ እንደምትችሉ፡ እምነት ከተሰማችሁ፡ ጥሩ ነው፥ ካልሆነ ግን፡ እንደሚፈውሳችሁ እመኑ። እምነታችሁ ያን ያህል ከሆነ፡ ያንን ወደ ውጭ ለማምጣት ረጅም ጊዜ ይወስድበታል፡ ኢየሱስ ግን፡ "እንደ እምነትህ፡ ይሁንልህ" ብሏል። አሁን ግን፡ ታላቅ እምነት ካላችሁ፡ ወዲያውኑ ልትፈወሱ ትችላላችሁ።

212 እዚህ ምርኩዝ የያዙ አንዳንድ ዓይነ ሰውራን ተቀምጠው አያለሁ፡ እንድታምኑ እፈልጋለሁ። ጉባኤው በሙሉ እኔ የምፈልጋችሁ... እዚህ የተቀመጠው አባትህ እና እናትህ ወይም ሌላ ሰው ቢሆንስ?

213 አሁን ቅኖች እንሁን። እኔ ማድረግ የምችለው ብቸኛው ነገር ሄጄ መጸለይ ነው። አሁን፡ ምን ችግር እንዳለና ምን እንደተፈጠረ ማወቅ ከፈለጉ፡ እግዚአብሔር ያንን ይገልጠዋል፡ ያ ይቻላል። ነገር ግን እንዲጸልዩላቸው ይፈልጋሉ፡ እኔም መጥቼ ብጸልይላቸው፡ እግዚአብሔር እንደሚፈውሳቸው ያምናሉ። እናም በሙሉ ልባቸው ካመኑት፡ አሁን እንደሚሆን አምናለሁ። እንግዲህ እነርሱ ይህን ካደረጉ...

214 እና አሁን ካልሆነ፡ ተስፋ አትቁረጡ፡ ምናልባት ከአሁኗ ጊዜ ጀምሮ—በግማሽ ሰዓት ውስጥ ሊሆን ይችላል፡ ምናልባት ከአንድ ሳምንት በኋላ ሊሆን ይችላል፡ እኔ አላውቅም፡ ካመናችሁ ግን ይሆናል። "እንደ እምነትህ፡ ይሁንልህ።" ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ፡ ጉባኤውም "አሜን፡" ይበል። አሁን በሙሉ ልባችሁ እመኑ።

215 ስንት ጊዜ ከእብድ ማቆያ ተቋም፡ በማሰሪያ ጃኬቶችና በመሳሰሉት ውስጥ ሆነው አይተናቸዋል፡ አሁን ግን ቤታቸው የሆኑ፡ ጤነኛ ሰዎችም የሆኑ፡ አያችሁ፡ ሁሉ ዓይነት በሽታዎችም ስንቴ አላየንምን?

216 አሁን፡ እኔ ስጸልይ አገልጋይ ወንድሞች ይጸልያሉ፥ ጉባኤውም ራሳችሁን ካጎነበሳችሁ፡ እንዲሁ ታደርጉ ይሆናል ብዬ እሰባለሁ። አንተም ወንድም ሆል፡ እዚህ ማይክሮፎኑ ጋር ቆይ። ልጄም፡ በመስመሩ ውስጥ አብረኸኝ ወደ ታች ውረድ።

217 እግዚአብሔር ልጄ ለታመሙ ሰዎች እንዲጸልይ እንዲጠራው እፈልጋለሁ። ለማጽናት መጀመሪያ የሆነ ነገር ሲከሰት ማየት እፈልጋለሁ፡ አያችሁ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ከእኔ ጋር እንዲሆን እፈልጋለሁ። እሺ።

(ከጉባኤውን አነጋገረው።) [ወንድም ብራንሃም ለሽባዎቹ ሲጸልይ ወንድም ሆል ለጉባኤው ተናገራቸው። በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

218 ክርስቲያን ወዳጆች ሆይ፡ በሙሉ ልባችሁ የምታምኑ ሁሉ፡ አሁን በተቻለ መጠን ሁሉም ሰው በመንፈስ ሁኑ፡ እግዚአብሔር ለፈውሳችሁ እያንዳንዳችሁን እንደባረከ አምናለሁ። እዚህ አንድ ዕውር የነበረ ሰው፡ ዓይኖቹን ወዲያና ወዲህ እየሞከረ ነው። እዚህ ሌላ ሴት እግሮቿን ከዊልቼር ውጭ

እያወጣች ነው፡ ጥቁር ሴት፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ከዚያ ላይ ትነሳለች። እዚህ ሌላ ሴት ተነሰታለች። በጣም ጥሩ። አሁን ሁሉም ሰው በመንፈስ ይሁን። መንፈስ ቅዱስ... ሰዎቹ እንደተባረኩ፡ በሙሉ ልቤ አምናለሁ።

219 አሁን፡ አድማጮች በሕንፃው ውስጥ ያላችሁ ሁሉ፡ እንድትቆሙ እፈልጋለሁ። አገልጋይ ወዳጆች፡ አሁን ወደ ፊት መጥታችሁ በ—በተጎዱት ላይ እጆቻችሁን እንድትጭኑ እፈልጋለሁ፡ እናንተ አገልጋይ ወንድሞቼ ሆይ፡ ወደ ፊት ቀርባችሁ እጃችሁን ጫኑባቸው፡ ከዊልቼሮች ተነስተው እንዲፈወሱ እምነታቸውን በመርዳት ልታግዟቸው ትችላላችሁ። አሁን፡ እኔ በምጸልይበት ጊዜ ሁሉም ሰው **እንደዚህ** እጆቹን ወደ እግዚአብሔር እንዲያነሳ እፈልጋለሁ።

220 አሁን፡ እመቤት፡ እዚህ ያለሽው ጥቁር ሴት፡ ከዚያ እንድትነሺ እፈልጋለሁ። እዚህ ያለሽው ሴትም፡ እዚያም ያላችሁ፡ አሁን በሙሉ ልባችሁ እንድታምኑ እፈልጋለሁ።

ክርስቲያኖች ሁሉ ጸልዩ።

221 አሁን፡ አባት ሆይ፡ ይህን አንድ ነገር በማወቅ፡ እነዚህን ሰዎች በስምህ ባርከናቸዋል “በጸለያችሁ ጊዜ፡ የፈለጋችሁትን ማናቸውንም ነገሮች፡ እንደተቀበላችሁ እመኑ” ብለህ ተስፋ ሰጥተሃልና። እዚያ በትንሿ ቃሬዛ ላይ ታስራና ተጣምማ የነበረችውን ያቺን ምስኪን ሴት ከዚያች አልጋ ላይ ማንሳት ከቻልህ፡ እያንዳንዳቸውን ማንሳት ትችላለህ፡ ጌታ ሆይ። አሁን ይፈወሱና ጤነኛ ይሁኑልን። አባት ሆይ፡ የትሑት አገልጋይህን ጸሎት ሰማ። አሁን፡ ጌታ ሆይ፡ አድርግልን።

222 ሰይጣን፡ እነዚህን ሰዎች ያሰርካቸው አንተ፡ እነሆ ተጸልዮላቸዋል፡ የእግዚአብሔር በረከት በላያቸው ላይ ተጠይቋል፡ አንተ ተሸንፈሃል።

223 በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ከዚያ ተነሺ! እነሆ፡ ሽባ የሆነች ሴት፡ ከወንበሩ ወጥታ፡ ተነስታ፡ ቆመች። ተመልከቱ፡ ከዊልቼር ተነስታ፡ ያለምንም እየተራመደች... ጌታ ይባረክ! እነሆ ሌላ ሴት ብቅ አለች፡ በዊልቸር ላይ ሽባ የሆነች ሌላ ሴት፡ ቆማ፡ እግዚአብሔርን እያመሰገነች ነው። እጃችንን ወደ ላይ እንስተን፡ በሁሉም እግዚአብሔርን እናመስግን። በትክክል። እዚያ ተነስ። በጌታ በኢየሱስ ስም፡ በእግርህ ቁም! ልጄ ሆይ፡ እጅህን ወደዚያ ዘርጋና ተፈወስ። የዊልቸር ወንበሮች ወደ ኋላ ተንቀሳቅሰዋል። ሰዎች በዊልቸር ወንበሮች ላይ፡ ወድቀው፡ አስደናቂ ነገር እየሆነ ነው... ሃሌ ሉያ! እግዚአብሔር ይመስገን!

51-0505 ተልዕኮዬ
ካልቫርይ ቴምፕል
ሎስ አንጀለሰ, ካሊፎርኒያ ዩ.ኤሰ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰሩ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org